# አለም አቀፍ የአጠባበቅ ማእቀፍ
# ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት
# ጥሰቶችን መከላከል
# አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ተገልጋዩች ተሞክሮ

**አላማ**

በአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ትርጉም መሰረት ከለላ ማለት የሰራተኞች እና የተገልጋዩች ጥበቃ፣ ደህንነት፣ እና ክብር ማለት ነዉ። ከተገልጋዩች አውድ ሲታይ፣ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ተገልጋዩች የሆኑ ወይም ሊሆኑ ያሉ አዋቂዎች ወይም ልጆች በድርጅቱ ሰራኞች፣ በተቋራጮች፣ በአጋር ድርጅቶች፣ በንዑስ-ተለጋሾች፣ በአቅራቢዎች ወይም በሌሎች አጋር አካላት ሊፈጸሙባቸዉ የሚችሉ አካላዊ፣ ንግግራዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃትን ያጠቃልላል። ይህ የአጠባበቅ ማእቀፍ በተለይ ተግባራዊ የሚሆነዉ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ተገልጋዩች ለሆኑ ወይም ሊሆኑ በሚችሉ አዋቂዎች እና ልጆች ላይ ነዉ።

ይህ የአጠባበቅ ማእቀፍ የተዘጋጀዉ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ጽ/ቤት የ መብት ጥሰቶችን በመከላከልና እልባት በመስጠት ረገድ ፈጣንና አግባብነት ያለዉ ዉሳኔ ለመወሰን እንዲረዳ ነዉ። ማእቀፉ በተዋረድ ለሚገኙ እንደ ረጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሼቲቭ (RAI) እና ክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፕመንት(CRRD )የመሳሰሉ ጽ/ቤቶች ሁኔታዎችን ያገናዘበ እና አካባቢን መሰረት ያደረጉ የቅድመ አደጋ ጥንቃቄዎች እንዲያደርጉ እንዲሁም የመከላከል ሂደትን ለማገዝ ይረዳል።

ሁሉም የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ጽ/ቤቶች የስራ እንቅስቃሴያቸዉን ሊያግዝ የሚችል መደበኛ የአተገባበር መመሪያ እንዲኖራቸዉ ይህንን የአጠባበቅ ማእቀፍ ሰራተኞቻቸዉ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ መሰረት በማድረግ መጠቀም አለባቸዉ።[1] ይህ ስነድ አነስተኛ ደረጃ ሊባል በሚችል መልኩ የአጠባበቅ ጥሰቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሲሆን የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴን መሰረታዊ እሴቶች፤ ፖሊሲዎች ታሳቢ ያደረገና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑትን ማእከል ያደረገ ነዉ። የአተገባበሩ ሁኔታ አካባቢን መሰረት ያደረጉ ህጎችን እና የድጋፍ አገልግሎት መስጫ የአቅርቦት ሁኔታን መሰረት አድርጎ በተጨባጭ ሊለያይ ይችላል።

ይህን የአጠባበቅ ማእቀፍ በአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ሰራተኞች በኩል እንግልት እና ብዝበዛ ለደረሰባቸዉ አዋቂዎችና ልጆች ተግባራዊ ይሆናል። ከልጆች ጋር በተያያዘ የተወሰዱ ተጨባጭ እርምጃዎችና ዉሳኔዎች የተለያዩ ከሆነ በሰነዱ ዉስጥ ባሉ የሳጥን ምልክቶች ዉስጥ መለያ ምልክት ሊደረግበት ይችላል። በተለየ መልኩ ካልተገለፀ በስተቀር ለአዋቂዎችም ሆነ ለልጆች የሚወሰዱ እርምጃዎች እና ዉሳኔዎች አንድ ዓይነት እንደሆኑ ይቆያሉ።

የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ የጥምር ግብረ ሀይል እየመራ ባለበት ጊዜ ወይም አጋሮች ተገቢ የምላሽ ስልቶች እና ፕሮቶኮሎች በቦታው ከሌላቸዉ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ይህንን የአጠባበቅ ማዕቀፍ እና መደበኛ የአተገባበር መመሪያ ለአጋሮቹ ሊያጋራቸዉ ይችላል። በተጨማሪም የራሳቸዉን የአሰራር ሂደት እስከሚዘረጉ ድረስ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ አጋሮችን በአጠባበቅ ፕሮቶኮሎች አግባብ ዉስጥ ሊያካትታቸዉ ይችላል።

> ይህ ስነድ ለረጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሼቲቭ (RAI) እና ክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፕመንት (CRRD) በተመሳሳይ መልኩ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ምንም እንኳን ረጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሼቲቭ (RAI) እሚተገበርባቸዉ አካባቢዎች በደንብ የዳበረ፤ አካባቢያዊ ሁኔታን ታሳቢ ያደረጉ ስልቶችን ተግባራዊ ሊያደርጉ ቢችሉም እነዚህ ጽ/ቤቶች ግልጽ የሆነ የዘገባና ምላሽ የመስጠት ሂደቶችና የመረጃ መለዋወጫ ፕሮቶኮሎች እንዲሁም ጠንካራ የሆነ የመከላከል ትግበራ መኖራቸዉን ማረጋገጥ መቻል አለባቸዉ።

ይህ የአጠባበቅ ማዕቀፍ የሚከተሉትን ክፍሎች ያካትታል፡-

I. መከላከል እና ዝግጁነት

1 መደበኛ የአሰራር ሂደት አብነት እዚህ ይገኛል፤ https://rescue.box.com/s/9xujls8skyqjrhe9gkcoq3xah9obj8jz

i. ግንኙነት/ተግባቦት

ii. ስልጠና

II. ሪፖርት አደራረግ

III. የሪፖርት በፍጥነት ወደ ላይ ማሳደግ/ማስተላለፍ እና የምርመራ ሂደት

IV. የምላሽ እና የድጋፍ አገልግሎቶች

V. መማር እና ሀሳብን ማንፀባረቅ

**መከላከል እና ዝግጁነት**

የአጠባበቅ ማእቀፍ ስለመኖሩ እና ስለይዘቱ እንዲሁም መደበኛ አከባቢያዊ የአሰራር ሂደቶች እና ለተገልጋዩች ደህንነት ከለላ ለመስጠት ታስበዉ የተዘጋጁ ሌሎች ሰነዶችን በተመለከተ ግንዛቤ እና አረዳድ መኖር ጥሰቶችን ለመከላከል ጠቃሚ መሰረታዊ ነገሮች ናቸዉ። አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ተቀባይነት ስላላቸዉ እና ስለሌላቸዉ የባህሪያት አይነቶች እንዲሁም የኮሚቴው የአጠባበቅ ፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ማእቀፎች ሲጣሱ በሁሉም ቢሮዎች ያሉ አመራሮች ለሰራተኞች መልእክት እንዲያስተላልፉ ይጠብቃል።[2] ይኽም በተጨማሪ ድንገተኛ ችግሮች ሲከሰቱ ወቅቱን የጠበቀ እና አግባብነት ያለዉ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁነትን ያረጋግጣል።

ግንኙነት/ተግባቦት

ግንኙነት ሲባል እንደ ድጋፍ ሰጪ፣ጊዜያዊ፣ ተቋራጭ፣ የቀን ሠራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አጋሮች፣ አቅራቢዎች፣ ወይም ሌሎች ተባባሪ ሠራተኞች እና ተገልግዩችን ጨምሮ ቋሚ ሠራተኞች ሊያከብሯቸዉ የሚገቡ ተጠባቂ ባህርያትን ስለማስቀመጥ ነዉ። ግልጽ፤ አጭርና ለመረዳት በማያስቸግር መልኩ ስለተጠባቂ ሁኔታዎችና ገደቦች ግንዛቤን ይፈጥራል፤ ተቀባይነት ስለሚኖራቸዉና ስለማይኖራቸዉ ባህሪያት ስርዐትን ይዘረጋል። በአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ በኩል እየተተገበሩ በሚገኙ አጠባበቆች ዙሪያ ጽ/ቤታችሁ ግልጽ የሆነ የግንኙነት አቅጣጫ እንዲኖረዉ የሚከተሉትን መሰረታዊ መመዘኛዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡-

- የአጠባበቅ አመራሮች በአካባቢያችሁ ማቋቋም
    - እነዚህ ሰዎች የቴክኒክ ሰራተኞች መሆን አይጠበቅባቸዉም፤ ነገር ግን ለስራዉ በጣም ተገቢነት ያላቸዉ ግለሰቦች መሆን ይገባቸዋል። የአመራሮች የስራ ድርሻ፤ ለምሳሌ የተገልጋዩች የአጠባበቅ ጥሰት በተመለከተ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መደበኛ የአሰራር ሂደትን ዝግጅት የመሰሰሉትን የአጠባበቅ ትግበራዎችን ወደታች በማዉረድ በኩል ድጋፍ ማድረግ ነዉ፤። አባሪ 1 ለ አመራሮች የተዘጋጀዉን የማጣቀሻ አተገባበር (ተርምስ ኦፍ ሪፈረንስ((TOR) ያስቀምጣል።
    - ለሴቶች ሠራተኞች እና ተገልጋዩች ሪፖርት እንዲያደርጉ፤ ድጋፍ እንዲሹ፤ በመከላከል ሂደቶች እና በመልእክት ልዉዉጥ ላይ ተፅእኖ እንዲኖራቸዉ ደህንነቱ የተጠበቀ መግቢያነት እንዲፈጠር ምንጊዜም ቢሆን ከአጠባበቅ አመራር መካከል ቢያንስ አንድ ሴት መኖሯን ያረጋግጡ።
    - ከተቻለ የተለያዩ አካባቢዎችን ለምሳሌ ዋና ከተማ እና በመስክ ቦታዎችን የሚወክሉ የጾታ ስብጥርን ያላቸው በዛ ያሉ የአጠባበቅ አመራሮች ይመድቡ።
    - ከአካባቢዉ ሰራተኞች ቡድን አመራሮች ውስጥ የአጠባበቅ አመራሮችን ይመድቡ፡ እነዚህ ግለሰቦች በከፍተኛ አመራሮች ቡድን ዉስጥ ወይም በሌሎች አካባቢያዊ ከፍተኛ አመራሮች ወይም የአመራር ቡድን ዉስጥ መቀመጫ እንዲኖራቸዉ ማድረግ ሚናቸው እና የደህንነት አጠባበቅ በአካባቢያቸው ትኩረት እንደተሰጠዉ ጠንካራ መልእክት ያስተላልፋል።

- ለሁሉም ሰራተኞች እና ተገልጋዩች ስለ አጠባበቅ ማእቀፉ፤ ስለ መደበኛ የአሰራር ሂደት እና የ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ የአጠባበቅ ፖሊሲዎች ይዘት ግልጽ ማድረግ እንደሁም፤ ተጽእኖ ከመፍጠር አንጻር፤ ትኩረት በተደረገባቸዉ አድማጮች በኩል አግባብ ያለዉ ስልጣንና ተአማኒነት ያለዉ መሆኑን በማረጋገጥ እነዚህን መልእክቶች ማን ሊያስተላልፍ እንደሚችል መለየት።
    - መደበኛ የሆነ የአሰራር ሂደትን በመዘርጋት እንዲሁም ለሌሎች ሰራተኞች እና ተገልጋዩች በማስተዋወቅ ሂደት ወቅት ሁሉም የአካባቢዉ ሴቶች እና ወንዶች፤ ሰራተኞች መሳተፍ

---

[2] እነዚህ የተገልጋዩች የአጠባበቅ ፖሊሲዎች፡- የሕፃናት ደህንነት ጥበቃ ፖሊሲ፤ እና ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጥበቃ ተጠቃሚዎች ፖሊሲ ናቸው።

ይጠበቅባቸዋል። ይህም በክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፕመንት(CRRD) የሥራ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ሴቶችን ማካተት አለበት ። ይህም አካባቢያዊ ቋንቋዎች እና ሁኔታዎች ግምት ዉስጥ መግባታቸዉን ለማረጋገጥ ይረዳል።

- በተጨማሪም የአካባቢያዊ ሰራተኞች ስብጥር፣ ከሥርዓተ-ጾታ ባሻገር ፣ብሔረሰባቸውን፣ ሀይማኖታቸውን ጨምሮ ሌሎች መለያ ባህሪያትን የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ሰራተኞችን ብዝሀነት ዉክልና ሰፋ አድርጎ የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ያስፈልጋል።

  - ከተገልጋዩች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እየተተገበሩ ያሉ ነባር መርሀ ግብሮችን እና የመርሀ ግብር ሰራተኞችን እንደ መነሻ መጠቀም ይመከራል።
  - መደበኛ በሆኑ የስራ ሂደቶች ላይ ቀላል እና ግልጽ የሆነ ቋንቋ መጠቀም ይመከራል፤ በተጨማሪም የጽሁፉ አርቃቂ ድርጅቱን ሊለቅ እንደሚችል ታሳቢ ባደረገ መልኩ መጻፍ አለበት፣ ይህም ሌላ ተጨማሪ ማብራሪያ ሳያስፈልገዉ ሰነዱ ራሱን ችሎ እንዲቆም ይረዳል።
  - ከተገልጋዩች ጋር አግባብነት ያለዉ የግንኙነት መስመር ለመዘርጋት እና ምክክር ለማድረግ እንዲረዳ ከቴክኒክ ባለሙያዎች የአጠባበቅን፤ የስርአተ ጾታ እኩልነትን፤ የጥቃት መከላከል እና ምላሽ ሰጭ ማእከልን(VPRU) በተመለከተ እንደየአስፈላጊነቱ ድጋፍ ጠይቅ ።

- ምን አይነት የግንኙነት መንገዶች ጥቅም ላይ እንደሚዉሉ ይለዩ ። በአካል በመገኘት ከሚደረጉ ግንኙነቶች በተጨማሪ ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያክል እንደ ፓስተሮች፤ የራዲዮ መልእክት እና ቪድዮ የመሰሰሉ ብዙ አይነት የመገናኛ አማራጮች አሉ።
  - ሁሉም ሰራተኞች እና ተገልጋዩች አጠባበቅን በተመለከተ ምን አይነት የግንኙነት ዘዴዎችን እንደሚመርጡ ማማከር የግድ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ከአካባቢያዊ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ዉስንነቶች፤ ለምሳሌ የሕዋስ አገልግሎት አለመኖር ወይም ጽሁፍ የሌላቸዉ ቋንቋዎች ግምት ዉስጥ መግባት አለባቸዉ። የተለያዩ አውዶቻችን ላይ እንዴት መግባባት አለብን ለሚለው አንድ ወጥ ትክክለኛ መልስ የለም፣ ዋናው ጉዳይ መልእክቱ እንዴት ተላለፈ ሳይሆን እንዴት ተቀባይነት አገኘ ነው። ፡
  - የጾታ እና የእድሜ ትንታኔን ለሚታሰበው የተለያየ የግንኙነት መንገድ አካል ማድረግ የግድ ያስፈልጋል፣ በተጨማሪም ጥቅም ላይ የሚዉሉት የግንኙነት ዘዴዎች እነዚህን መስል ልዩ ቡድኖች ፍላጎት ያንፀባረቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ከቡድኖቹ ጋር ምክክር መደረግ አለበት።

> አስታዉሱ፡- በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ የሚገኙ ልጆች እና አዋቂዎች ሙሉ በሙሉ በጽሁፍ የቀረበን ፓስተር ላይረዱ ይችላሉ። ምናባዊ ፤ ካርቱን፣ቪድዮዎችን ወይም ሌሎች መልእክቶቻችንን ሊያስተላልፋልን የሚችሉ ዘዴዎችን መጠቀም ረገድ የፈጠራ ችሎታ ሊኖረን ይገባል።

- ስለ አጠባበቅ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሂደት (SOP) መደበኛ የሆኑ ማስታወሻዎች ፣ ግንኙነቶች እንዲሁም ሌሎች ተዘማች ግብአቶ ችን ያዘጋጁ።
  - የአጠባበቅ መሪዎች በሌሎች የበላይ አመራር አባላት ታግዘው ከሁሉም ሰራተኛ ጋር ስለ ተገልጋዮች ደህንነት ዘወትር የሚነጋገሩበት መንገድ እንዲያዘጋጁ ይመከራል። ይህም በከፍተኛ አመራር ደረጃ ተጨማሪ የውይይት ርእሶችን በማከል ወይም በሁሉም ሰራተኞች ስብሰባ ላይ፣ በየሩብ ዓመቱ በተለያዩ የአያያዝ ዘርፎች ማነቃቂያዎች ወይም የሚነበቡ ጹሑፎች በየቢሮው እንዲገኝ በማድረግ ላይ ትኩረት በመስጠት ሊሆን ይችላል። የተለያዩ ዘዴዎች ውህደት የበለጠ ውጤታማ የመሆን እድሉ ስፊ ነው።
  - የቴክኒክ ሰራተኞች የአጠባበቅን፣ ወጣት ሴቶችን የማብቃት፣ የጥቃት መከላከል እና ምላሽ ክፍልን (VPRU) ተገቢ የግንኙነት ግብአቶችን ለማዳበር የሚያግዝ ልዩ ክህሎት ስላላቸው ምሪት ከእነርሱ መሻት ይመከራል። እ.ኤ.አ. በ 2018 በ ዓለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የተቋቋመው የአጠባበቅ ግብረ ኃይል ከክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፕመንት(CRRD) እና ሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሽቲብ(RAI) የተውጣጡ የቴክኒክ ሰራተኞች እና የከፍተኛ አመራሮችን የያዘ ስብጥር ሲሆን በየሁለት ወሩ የሚያዘጋጅው የአጠባበቅ ግንኙነት ግብአት ለዚህ ስራ ሊያግዝ ይችላል።

<u>ስልጠና</u>

ግንኙነት ቃናን እና ባህሪን ስለማዘጋጀት ሲሆን ስልጠና ደግሞ ቋሚ ሰራተኞች እና ማበረታቻን ፣ ጊዜያዊ፣ተቋራጭ ፣ የቀን ሠራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አጋሮች፣ ሻጮችን፣ ወይም ሌሎች ተባባሪዎችን ተቀባይነት ያለው ባህሪ ምንነት ጠለቅ ባለ መልኩ እንዲረዱ እውቀት እና ክህሎት ስለማስጨበጥ ነው። |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||In particular, this tells us *why* the IRC believes some behaviors are acceptable for anyone associated with the organization – like treating clients with respect and dignity – and others – like the use of child labor preventing children from accessing their full educational potential – is not acceptable.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

ከዚህም በተጨማሪ ስልጠናው ግለሰቦች የአጠባበቅ ጥሰት ቢፈጸምባቸው በወቅቱ፣ በአክብሮት እና ከጥቃት የተረፉትን ያማከለ አግባብ ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ እውቀት እና ክህሎትን ማስጨበጥ ነው። ማንም ሰው በደመ ነፍስ ለጥቃት ለተረፈው ግለሰብ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለበት ማወቅ አይጠበቅበትም። በአንዳንድ አካባቢያዊ ቢሮዎች በዚህ ርእስ ላይ የሰለጠኑ ሰራተኞች ሊኖሩ ይችላል፣ ይህም ጠቃሚ እሴት እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ፤ ነገር ግን ከተቻለ ሁሉም ሰራተኞች እንዴት ለጥቃት ተራፊው ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ስልጠና መውሰድ ይገባቸዋል። ከጥቃት ተራፊው ይፋ ከመሆን ጋር ማንን ማመን እንዳለብን ስለማናውቅ ሪፓርት የማድረግ አቅም ያለን ወደፊት በመምጣት ሁሌም የጥቃት ተራፊውን ለማገዝ ዝግጁ መሆን አለብን።

ስልጠናዎቹ የግድ መሰጠት ያለባቸው ሶስት ደረጃዎች አላቸው

1) የጥቃት ተራፊው ይፋ በሚሆንበት ጊዜ እንዴት እና ምን አይነት የመጀመሪያ ደረጃ ስነልቦናዊ እርዳታን የማድረግንጨምሮ አፋጣኝ እና ቀዳሚ ምላሽ እንደሚስጥ ፣ወደ ክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፕመንት( CRRD ) ቢሮ ጉዳይ ተከታታይ ስራተኛ ወይም ሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሽቲብ ( RAI) የውጪ ድጋፍ አገልግሎት ሰጭ ሪፈራል እንደሚደረግ ፣ ምን እና እንዴት መመዝገብ ወይም ሪፖርት እንደሚደረግ፣ የምስጢራዊነት መርሆችን እና ፈቃደኝነት እንደሚሰጥ ሁሉም ሰው ማወቅ አለበት።
2) የአመራር እና የአጠባበቅ ቀዳሚ መሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ሊሰለጥኑ ፣ በተጨማሪም የግንዛቤ መስጨበጫ እና የባህርይ ለውጥ የማምጣት እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል ክህሎት እና እውቀት ሊሰጣቸው ይገባል።እንዲሁም
3) የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኞች ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች እና አነስተኛ የምላሽ አሰጣጥ አገልግሎት ላይ መሰልጠን አለባቸው።

- ቋሚ ሰራተኞች ፣ ማበረታቻን ፣ጊዜያዊ፣ ተቋራጭ፣ የቀን ሠራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አጋሮች፣ ሻጮች፣ ወይም ሌሎች ተባባሪዎች ፣ ጨምሮ ስለ አጠባበቅ ማዕቀፍ እና መደበኛ የአሰራር ሂደት ላይ ጠቅላላ ግንዛቤ እንዳላቸው ለማረጋገጥ እቅድ ማዘጋጀት እና ስልጠና መስጠት በተጨማሪም ከኮሚቴው ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ሁሉ ተቀባይነት ስላለው ባህርይ ምንነት ማስታወሻ እና ማነቃቅያ እንዲሆናቸው ስልጠናዎችን ማግኘት አለባቸው።
    - በዋና ጽ/ቤት ደረጃ በአካባቢያዊ አገባብ/አንፃር እና አተገባበር ያካተተ የአጠባበቅ ስልጠና ጥቅል እየተዘጋጀ ነው። ጥቅሉም የኢ-ትምህርት ሞጁሎችን እና የአሰልጣኝ አሰልጣኞችን የሥልጠና ቁሳቁሶችን ያካተተ ሲሆን ቀስ በቀስ እውቀትንና ክህሎትን ለመገንባት እና ከጊዜ በኋላ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት እንዲያስችል ተደርጎ የተቀረፀ ነው። ስለ ስልጠና ጥቅሉ እና እድገቱ ስለሚገኝበት ደረጃ መረጃ ከአጠባበቅ ዳይሬክተሩ ማግኘት ይቻላል። ስልጠናዎቹ ተሻጋሪ አውዶች ላይ ለመናገር እንዲያስችሉ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው ፣ ሆኖም ግን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ አውድ እና ትርጉም ሊዳብር ይገባል። ዝግጅቱ ተጠናቆ ከወጣ ስልጠናው በሁሉም ሥፍራ ላሉ የድርጅቱ ሠራተኞች ሁሉ መሰጠት አለበት ።
    - በተቻለ መጠን በሂደት ላይ ያሉ የውስጥ ሰራተኞች አቅም ግንባታ እንዲሁም ሌሎች የአጠባበቅ እና ከአስተማማኝነት ጋር የተዛመዱ ተግባራትን ለሚሰሩ፣ ለቋሚ ሰራተኞች፣ ማበረታቻን ፣ጊዜያዊ፣ ተቋራጭ፣ የቀን ሠራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አጋሮች፣ሻጮች፣ ወይም ሌሎች ተባባሪዎችን ጨምሮ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ለማከናወን የገንዘብ ድጋፍ መጠየቅ ይመከራል። ከዚህ ጋር በቀጥታ ለተገናኘ እንቅስቃሴ በግለሰብ ደረጃም ቢሆን የገንዘብ ድጋፍ ሊሰጥ እንደሚችል በአሁኑ ወቅት አመላካች ሁኔታዎች አሉ።
    - ከአጠባበቅ፣ወጣት ሴቶችን የማብቃት፣ የጥቃት መከላከል እና ምላሽ ክፍል እንደአስፈላጊነቱ የስልጠና ግብአቶችን ተስማሚ ለማድረግ ወይም ለማዳረስ ከቴክኒክ ባለሙያዎች ድጋፍ ይሹ።

***ሪፖርት አደራረግ***

ለዓለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ተገልጋዩች አግባብ ያለው ፣ ደህንነት ፣ ክብር እና ፣ በሚስጢራዊነቱን በተጠበቀ እንዲሁም ከጥቃት የተረፈን ባማከለ ሁኔታ ለድርጅቱ ሪፖርት የማድረግ አቅም መኖር ጥቃት እንደተፀመ ፈ እንዲታወቅና እና መፍትኄ እንዲያገኝ አስፈላጊ ነው። የሪፖርት ማድረጊያ ስልቶች መኖር ብሎም መገልገል ግልፅ የሆነ እና ለግንኙነት አመቺ የሆነ ሁኔታን በመፍጠር ብቻ ሳይሆን የኃላ ኃላ አጥፊዎችንም ለመከላከል ይረዳል።

የሪፖርት ማድረግያ መንገዶቹ ከአሰራር አንፃር/አውድ ስለሚለያዩ የጾታ እና እድሜ ልዩነት ላላቸው ተገልጋዮች ተደራሽ የሆኑ ልዩ ልዩ ሪፖርት ማድረግያ መንገዶች ሊዘጋጁ ይገባል። ትልቅ ቦታ ሊሰጥ የሚገባውም ተግባር ላይ የዋለው አሰራር ለተቋሙ ብቻ ሳይሆን ለተገልጋይ ማህበረሰብም ተስማሚ መሆን ይገባዋል።[3] የዓለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የህጻናት ጥበቃ፣ የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ (WPE) ወይም የህግ ጥበቃና የበላይነት (PRoL) ፕሮግራሞች በተግባር ላይ ከሆኑ ተቋማቱን ሪፖርት ለማድረግ መጠቀም የሚበረታታ ሲሆን በእነርሱም በኩል ሪፖርት የመተላለፍ እድሉም የሰፋ ነው። የእነዚህ ተቋማት እንቅስቃሴ የተገደበ ወይም እንደተጨማሪ ብቻ በሆኑበት ጊዜ ሌሎች ማስተላለፊያ መንገዶች መፈጠር አለባቸው። የዓለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ በጋራ ወይም በጥምረት የተጠቃሚዎች ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጥበቃ (Beneficiary Protection from Sexual Exploitation and Abuse-PSEA) አቤቱታ መስማት የመሳስሉ ስልቶች ላይ ተሳታፊ ከሆነ ተገልጋዩች ይኸንን ስልት በመጠቀም የብዝበዛ እና ጥቃት ክስተቶችን በቀጥታ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

- ለተገልጋዩ ማኅበረሰብ አመቺ የሆኑ ሪፖርት ማድረግያ ስልቶችን መፍጠር።
    - ተገልጋዩ ማህበረሰብ የዓለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የፕሮግራም አወጣጥ ፣ የታማኝነት ወይም የአጠባበቅ ጥሰቶችን ላይ ያሏቸውን አቤቱታዎች ሪፖርት ለማድረግ የሚመርጡትን የተሻለ መንገድ ለመለየት ግምገማ እንዲያደርጉ ይመከራል።
    - የሪፖርት ማድረጊያ ስልቶች የተለያዩ ቅርጾችን ሊይዙ እና በእንቅስቃሴዎ አንፃር/አውድ ማለትም በአከባቢ ፣ በእድሜ ፣ በሃይማኖት ፣ በጎሳ ክፍፍል እና በጾታ እንኳን ሊለያዩ እንደሚችሉ ያስታውሱ። የሪፖርት ማድረጊያ ስልቶች በሚቀረጽበት ወቅት ቋንቋ እና ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። በተጨማሪም ሪፖርት የማድረጊያ መሥፈርቶች በአንድ ሀገር ወይም ከተማ ውስጥም እንኳን ሊለያይ ይችላል። ግምገማዎች ሲደረጉ እነዚህን ልዩነቶች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል።

- የሪፖርት አደራርግ ስልቶች ተግባር ላይ እንዲውሉ ዕቅድ መንደፍ እና የዕቅድ ሥርዓቱ ስለመኖሩም በቋሚነት ለሚመለከታቸው የማህበረሰብ ክፍሎች መግለጽ ያስፈልጋል።
    - የሪፖርት አደራረግ ስልቶች ተግባር ላይ በሚውሉበት ወቅት ከሚመለከታቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በመረዳዳት እና በመቀናጀት እንዲሆን ያስፈልጋል። ይህም ከመነሻው ጀምሮ የሪፖርት አደራረግ ስልት ላይ መተማመን እንዲኖር እና ስርዓቱ ለሚመለከታቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጠቀሜታ መሆኑን እንዲረዱ ለማረጋገጥ ይረዳል።
    - የምስል ፣ ድምጽ እና ቪዲዮ ግንኙነተኞች (እንደ አግባብነቱ እና የገንዘብ አቅም በሚፈቅደውን መጠን) ባህላዊ አግባብ እና ቋንቋን ያማከሉ እንዲሁም በተቻለ መጠን ለልጆች እና ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ተገልጋዩች እይታ አመቺ እና ሪፓርት አደራረግ በቀላሉ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል።
    - የሪፖርት አደራረግ ስልቶቹ መልካም ተሞክሮን እና ዒላማ የተደረጉ ክፍሎችን ፍላጎቶች የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ በአጠባበቅ ፣ልጃገረዶችን የማብቃት፣ ጥቃትን የመከላከል እና ምላሽ (VPRU) , እና የክትትል፣ ግምገማ እና መማር(Monitoring Evaluation and Learning (MEAL)) የቴክኒክ ባለሙያዎች ዘንድ ድጋፍ ማግኘት ይመከራል።

[3] በተገልጋዩች ሪፖርት ማድረጊያ ስልቶች ላይ ተጨማሪ መመሪያ ከደንበኛ ምላሽ ሰጪ ማዕቀፍ (CRF) ወይም የሰነ ምግባር እና ተስማሚነት ክፍል /ኢቲክስ እና ኮምፕሊያንስ ዩኒት(ECU) አመራሮች ማግኘት ይቻላል። |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Current draft of the guidance note, templates, and existing good practices can be found here: https://rescue.box.com/s/645zwce8mr9xhenbqg0z1hky8cwhthvd|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

- በሪፖርት አደራረግ ሥርዓት አጠቃቀም ላይ የክትትል ሥርዓት ማበጀት እንዲሁም ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ፍላጎት የተመቸ ሆኖ እንዲዘልቅ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
    - የሪፖርት አደራረግ ሥርዓቱን ውጤታማነት ለማወቅና ሪፖርቶችን ለማግኘትም እንዲቻል ከተጠቃሚው ማህበረሰብ ጋር መደበኛ የግብረ መልስ ስብሰባዎችን ማካሄድ ያስፈልጋል።
    - ከተገልጋዩች ጋር በቀጥታ እና በየጊዜው ግንኙነት የሚያደርጉ በመሆኑ የ የክትትል፣ ግምገማ እና መማር እና የመርሃ ግብር ሠራተኞች በረጅም ጊዜ የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቱ የቁጥጥር ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ይመከራል። ይህን ሥራ የመምራትና ሥራ ላይ መዋሉንም የማረጋገጥ ተግባር በአካባቢ ደረጃ የሚገኙ ከፍተኛ የአመራር ሠራተኞች ሃላፊነት ነው።

**የሪፖርት በፍጥነት ከፍ ማድረግ እና የምርመራ ሂደት**

አለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ተገልጋዮች የሠራተኞቹን የሥነ-ምግባር ጉድለት ለመግለጽ ሥጋት እንዳይኖርባቸው ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር የሚፈልግ ከሆነ ሪፖርቶችን ሪፖርቱን የሚደርገው ሰው ማንነት ምስጢራዊነት እና ደህንነት እንዳይገለጽ በሚያደርግ መልኩ የተቀበለ መሆኑን ማረጋገጥ የግድ ያስፈልገዋል ። በአንዳንድ አለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች ባለው ነባራዊ ሁኔታ ለጥቃት ተጋላጭ የሆነ ሰው የአጠባበቅ ጥሰት እየደረሰበት ስለመሆኑ ማህበረሰቡ ወይም ቤተሰቡ ሊያውቅ የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

> ልብ ይበሉ፡ የአጠባበቅ ጥሰቱ ሕጻናትን የሚመለከት ከሆነ አስገዳጅ የሆኑ የሪፖርት አደራረግ መሥፈርቶች ይኖራሉ።

ሪፖርት አደራረግ በአዋቂዎች፣ በወጣቶች እና በትንንሽ ልጆች መካከል ግልፅ ልዩነት የሚያደርግ ነው። ሕጻናት ሪፖርት ሲያደርጉ፣ የሪፖርታቸው ምሥጢራዊነት የህጻናቱን ሁለንተናዊ ጥቅም ከመጠበቅ ጋር ሚዛናዊ መሆን አለበት። በሪፖርት በሚደረግበት እና ምርመራ ሂደት በማናቸውም ወቅት ተንከባካቢያቸው ከሕጻናት አብሯቸው ሊኖር ይገባል።[4] ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ለሕጻናት ጥያቄ ሲቀርብላቸው ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፐመንት(CRRD)በተለይም የቻይልድ ፕሮቴክሽን ቴክኒካል ስታፍ (Child Protection Technical Staff) በተቻለ መጠን የተሻለው ዘዴ የቱ እንደሆን እንዲመክሩ ወይም እንዲሳተፉ ማድረግ በጥያቄ ሂደቱ ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ ይገባል።

ለሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሼቲቭ (RAI) የውጭ ምንጮችን መጠቀም አስፈላጊ ሊያደርገው ይችላል።

ሪፖርቱን በሚያዘጋጁበት ወቅት የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ሠራተኞች የሚከተሉትን መረጃዎች ማግኘት ይኖርባቸዋል፦ የተፈጸመው ድርጊት ምንድን ነው፣ ይህ የተባለው ጉዳይ መቼ እና የት ነው የተፈጸመው፣ እና በድርጊቱ የተሣተፈው ማን ነው። ሪፖርቱን የሚያደርጉት ሰዎች እየዋሹ ነው ወይም የፈጠራ ውንጀላ ነው ብሎ ሃሳብ ማቅረብ ተቀባይነት የለውም። ሪፖርት ቅበላ ወቅት ከጥቃት የተረፉ ሰዎችን አማካይ ያደረገ አግባብነት ያላቸውን ጥያቄዎችን ማቅረብ፣ ሪፖርት አድራጊውን ማመን እና ከዚያም መረጃውን ለምርመራ ለኢቲክስ እና ኮምፕሊያንስ ዩኒት (ECU) ማስተላለፍ ያስፈልጋል።

[5]ፈቃደኝነት እና ምሥጢር መጠበቅ [6]ለየአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ሪፖርት የሚያደርጉ ከጥቃት የተረፉ ሰዎችን ክብርና እንክብካቤ መስጠት ወሳኝ ጉዳይ ሲሆን ይህንንም ዘወትር ልንከተለው የሚገባ ነው። የአለም

---

[4] አገልግሎት ሰጪ/ተንከባካቢ ማለት ለህጻን ልጅ የዕለት ተዕለት እንክብካቤ የሚያደርገውን ግለሰብ የሚገልጽ ቃል ነው ። እሱ ወይም እሷ ወላጅ ፣ ዘመድ ፣ የቤተሰብ ጓደኛ ወይም ሌላ ሞግዚት ነው/ናት ፤ የግዴታ የሕግ ሀላፊነትን አያመለክትም።

[5] |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||In IRC, consent is defined as the voluntary agreement of an individual who has the legal capacity to give consent.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END||| የተረጋገጠ ስምምነት ለመስጠት፣ ግለሰቡ ስለሚቀርቡለት አገልግሎቶች ለማወቅ እና ለመገንዘብ እንዲሁም ሕጋዊ ፈቃዱን ለመስጠት አቅም እና ብስለት ሊኖረው ይገባል። ፈቃድ አሰጣጡ " በመረጃ የተደገፈ" መሆኑን ለማረጋገጥ፤ የአገልግሎት አቅራቢዎች ከጥቃት ለተረፈው ግለሰብ የሚከተሉትን መረጃዎች፦-እሷ/ እሱ ምርጫ ማድረግ እንድትችል/እንዲችል ያሉትን ሁሉንም መረጃዎችን እና አማራጮችን፤ የእሷን/የእሱን መረጃ ተጨማሪ አገልግሎት መስጠት ለሚችሉ ለሌሎች ሰዎች ማካፈል እንደሚያስፈልጋት/እንደሚያስፈልገው ማሳወቅ ፤ ከእሷ/ከእሱ ጋር አብረው ሲሰሩ ምን እንደሚሆን፤ የአገልግሎቶች ጥቅሞች እና ጉዳቶች ፤ እርሷ / እሱ ማንኛውንም የአገልግሎት ክፍሎች ያለመቀበል ወይም እምቢ የማለት መብት እንዳላት/እንዳለው ፣እና የምስጢራዊነትን ገደብ መስጠት አለባቸው።

[6] |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||In IRC, confidentiality is defined as ethical principle that is associated with medical and social service professions.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END||| ምስጢራዊነትን ለመጠበቅ፣ የአገልግሎት አቅራቢዎች ስለተገልጋዩቻቸው የተሰበሰበውን መረጃ እንዲጠብቁ እና የተገልጋያቸውን ጉዳይ የሚያጋሩት፣ ከተገልጋዩች በግልጽ በተሰጠ ፈቃድ መሰረት ብቻ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። ሁሉም የተፃፉ መረጃዎች ምስጢራዊ ቦታ በተቆለፉ ፋይሎች ውስጥ ተጠብቀው የሚቆዩ ሲሆን ጠቋሚ ያልሆኑ መረጃዎች ብቻ በጉዳይ ፋይሎች ላይ ይጻፋሉ ። ምስጢራዊነትን መጠበቅ ማለት፣አገልግሎት አቅራቢዎች

አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ከጥቃት የተረፉ ሰዎችን ማዕከል ያደረገ አካሄድ ይከተላል። ለዝርዝር መረጃ *የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴን ጋይድላይን ፎር ኤ ሰርቫይቨር ሴንተርድ አፕሮች ቱ ሪፓርቲንግ ሴፍጋርዲንግ ሚስኮንዳት (Guidelines for a Survivor-Centered Approach to Reporting Safeguarding Misconduct)* የሚለውን ይመልከቱ።

ጉዳቱን አድርሷል ተብሎ የተጠረጠረው ግለስብ የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ሠራተኛ ካልሆነ ኮሚቴው በውስጣዊ የአሰራር መንገድ ሪፖርቱን ያቀርባል ወይም ለተጨማሪ ምርመራ እና እርምጃ ጉዳዩን ለአካባቢው የሕግ አስከባሪ አካላት ያስተላልፋል። ይህ ጉዳዩን ወደሌላ አካል የማስተላለፍ ድርጊት ሊተገበር የሚችለው ግለሰቦች (ከጥቃት የተረፉ ሰዎች፣ ሠራተኞች፣ ወይም ምስክሮች) ለደህንነት ስጋት ወይም ለአደጋ የማይጋለጡ ከሆነ ብቻ ነው።

- በተገልጋዩች ላይ የደህንነት አጠባበቅ ጥሰት በሚፈጸምበት ወቅት ለኮሚቴው ሠራተኞች፣አብረታኞች፣ ጊዜያዊ ወይም ተቋራጭ ሠራተኞች፣ ለበጎ ፈቃደኞች፣ አጋሮች፣ አቅራቢዎች፣ ወይም ለሌሎች ተባባሪዎች ሪፖርቶችን እንዴት መቀበል እና ሪፓርት የተደረጉ ወይም የተመረጡ ክስተቶችን በፍጥነት ከፍ ማድረግ እንደሚገባ መግለጽ ይገባል።
  - እንደ እያንዳንዱ አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ እንዴት ሪፖርቶችን በፍጥነት ከፍ ማድረግ፣ የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ በአካባቢው እንዴት የአጠባበቅ ሥራ እንዴት እንደሚሰራ የሚያሳዩ የግንኙነቶችና የሥልጠና ክፍል አካል ማድረግ አስፈላጊ ነው።
  - |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Remember that reporting should follow our *Global Reporting Guidelines* and *IRC Guidelines for a Survivor-Centered Approach to Reporting Safeguarding Misconduct*. |||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||በሕጻናት ላይ የደህንነት አጠባበቅ ጥሰት በሚፈጸምበት ወቅት ሪፖርቶችን እንዴት መቀበልና እንዴት በፍጥነት ወደ ላይ ከፍ ማድረግ እንደሚገባ ተጨማሪ መመሪያ በአባሪ ማዕቀፉ (Handling Framework)ክፍል 2 ላይ ይገኛል ።
  - ተገልጋዩች ሪፖርት አደራረጋቸው ሥርዓት ከጥቃት የተረፋ ግለሰቦችን ማዕከል ያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ በአጠባበቅ፣ምርመራ ፣ልጃገረዶችን የማብቃት፣ ጥቃትን የመከላከል እና ምላሽ (VPRU) የቴክኒክ ባለሙያዎችን ድጋፍ ማግኘት ይገባል።

- በመርማሪ ቡድኑ የሚቀርቡ ሁሉም ጥያቄዎችና እንዲሁም ጉዳት አድርሰዋል ከተባሉ ተጠርጣሪዎች ፣ ከጥቃት ከተረፉ ሰዎች እና ለጋሽ አካላት ጋር የሚደረጉ አስፈላጊ ግንኙነቶች በጥንቃቄ የሚያዙ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የመረጃ አያያዝ ፕሮቶኮል ማዘጋጀት ያስፈልጋል።
  - እንደዚህ ዓይነቶቹ ግንኙነቶች ኃላፊነት ስለመውሰድ በከፍተኛ አመራሩ በቅድሚያ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ከእያንዳንዱ ልዩ ሁኔታ እና እንደ ከጥቃት የተረፉ ግለሰቦች ፍላጎቶች በመመርኮዝ እንዲሆን ያስፈልጋል።
  - ወቅታዊ እና ከጥቃት የተረፉ ሰዎችን ማዕከል ያደረገ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ እንዲቻል ሪፖርት ከመደረጉ በፊት ከተለያዩ ወሲባዊ ጥቃቶች ሪፖርት አደራረግ እና ተጠያቂነት ጋር ተዛማች የአከባቢያዊ ህጎች ትንታኔ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡
  - በእነዚህ ግንኙነቶች እና የክትትል ሥራዎች ላይ የአካባቢው የአጠባበቅ መሪዎች ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱ እንዲደረግ ይመከራል።

**የምላሽ እና የድጋፍ አገልግሎቶች**

|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||When violent safeguarding violations occur, IRC requires that offices be equipped to provide quality, gender- and age-appropriate services, and that medical care be available within 72 hours[7] alongside the other minimum response services as outlined below.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

---

የጉዳይን ዝርዝር ከቤተሰብ ወይም ከጓደኞች ጋር ወይም ስለ ደረሰው ጥቃት ማወቃቸው አላስፈላጊ ነው ከሚባሉ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በጭራሽ አይወያዩም ። ምስጢራዊነት ከልጆች ጋር በሚሰሩበት ወቅት ወሰን አለው።

[7] ከ 72 ሰዓቶች በፊት ቀደም ብሎ ቢሆን ተመራጭ ነው፣ እና ሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢን72 ሰዓቶች በፊት ቀደም ብሎ ቢሆን ተመራጭ ነው፣ እና ሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሽቲብ/ክልላዊ ፀረ-ሙስና ተነሳሽነት (RAI) ጨምሮ በአንዳንድ አገባቦች አፋጣኝ አገልግሎቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

የጤና፣ የሕጻናት ጥበቃ እና/ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ (WPE) የክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፐመንት (CRRD) ቢሮዎች ባሏቸው ነባሪ መርሃ ግብሮች፤ እነዚህ ዘርፎች በመልካም ተሞክሮዎችና በመርሃ ግብሮች አወጣጥ ደረጃዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ የጥራት ምላሽ አገልግሎቶችን ለማረጋገጥ ዋነኞቹ መሆን አለባቸው። ይህም አራት ሰፊ መደቦችን ፡- የደህንነት፣ የሕክምና፣ የሥነ-አዕምሮ፣ እና በተወሰነ ሁኔታዎች የሕግ አገልግሎቶች ያካትታል። ግልፅ የሆነ የሪፈራል መንገዶችን ለማቋቋም እና እነዚህን አገልግሎቶች እንዴት እንደምናቀርብ ለእያንዳንዳናቸው አገልግሎቶች መለስተኛ ደረጃዎች በአባሪ 3 ላይ በዝርዝር ተዘርዝረዋል፡

ማንኛውም የምላሽ እና ድጋፍ አገልግሎት በእያንዳንዱ ልዩ የአጠባበቅ ጉዳይ ላይ የህፃናት ጥበቃ (Child Protection) ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ(WPE) ጉዳይ ተከታታይ ሠራተኞች መመደብን ከጥቃት የተረፈው ግለሰብ እንደ አስፈላጊነቱ አፋጣኝ ምላሽ እና ድጋፍ ማግኘቱን ለማረጋገጥ የግድ መሆኑን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። እንደዚህ አይነት ሚናዎች በማይኖሩበት ጊዜ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ዝቅተኛ ደረጃችን ጋር የሚመጣጠኑ አማራጭ እርዳታ መጠየቂያ አሰራሮች እና በግልጽ የተደራጀ የሪፈራል መንገዶች ስራ ላይ እንደሆኑ የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት:

ለሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሼቲቭ (RAI)በአካባቢ ያሉ የእርዳታ አግልግሎት ሰጪዎች መኖር ሪፈራልን በእጅጉን ቀላል ያደርገዋል። የሆነ ሆኖ ፣ እነዚህ አገልግሎቶች በአባሪ 3 ውስጥ የተዘረዘሩትን ዝቅተኛ ደረጃዎች የሚያንፀባርቁ መሆናቸው አስፈላጊ ነው ፣ እነዚህም በአብዛኛዎቹ ከክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፐመንት (CRRD) መርሃግብሮች ውስጥ ያለውን የአገልግሎት ክፍተትን ለመቅረፍ የተፈጠሩ ሆኖ ከመልካም ልምዶች ጋር የተጣጣመ ግልፅ ደረጃን ያዘጋጃል። በሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሼቲቭ (Rai) እንኳን ቢሆን የደህንነት፣ የህክምና ፣ የሥነ-አዕምሮ ፣ እና በተወሰኑ ሁኔታዎች የሕግ አገልግሎቶች እንዲኖሩ እና በግልጽ የተደራጀ የሪፈራል አሰራሮች ቀደም ብሎ እንዲመሰረቱ እንፈልጋለን ::

- የአጠባበቅ ጥሰት ከመከሰቱ በፊት ተገቢ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ የሚያመለክቱ አጠቃላይ እይታ ወይም እቅድ አዘጋጁ ።
  - |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||It is required that the IRC's CRRD Rapid Service Mapping Tool or similar mapping tools be used.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END||| በአሰራር አካሄድ ላይ ለውጥ ሲኖር ፣ ከጥቃት የተረፉ እና ረዳቶቻቸዉ ሲፈልጉ እንዲጠቀሙባቸው አገልግሎቶቹ መኖራቸዉ ለማረጋገጥ የአገልግሎት ግምገማው እንደገና መከናወን አለበት ።
  - ለክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ዲቨሎፐመንት (CRRD):
    - ምንም የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ህጻናት ጥበቃ ፣ የጤና ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ (WPE) አገልግሎቶች በሌሉበት እና ቅርብ የሆነ የውጭ አገልግሎቶች ከሌሉ ወይም አጥጋቢ ጥራት ከሌላቸው ፣ የውስጥ ባለሙያን ለማምጣት ወይም የዉጭ አገልግሎት ሰጪዎችን አቅም ማጠንከሪያ እቅድ ማዉጣት ይጠበቃል::
    - ጉዳይ ተከታታዮች ከአጠባበቅ ጥሰት የተረፉ ግለሰቦች ጋር ለመስራት ቀድመዉ እንዲታወቁ ያስፈልጋል። እነዚህም ነባር የህጻናት ጥበቃ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ (WPE) ሰራተኞች ሲሆኑ፤ ምንም የህጻናት ጥበቃ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሃ ግብሮች ወይም ከዉጭ አገልግሎት ሰጪዎች በሌሉ ጊዜ ሌሎች አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ሠራተኞች እነርሱን ሊተኩ ይችላሉ ። ሌሎች የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ሠራተኞች ወይም የዉጪ አገልግሎት ሰጪዎች፣ በተመለከተ በቂ ስልጠና ሊሰጣቸዉ ይገባል::
    - በአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ላይ ውንጀላ ያቀረበ ከጥቃት የተረፈ ግለሰብ ከኮሚቴው እርዳታ ለመቀበል ምቾት የማይሰማው ከሆነ ከተቻለ የሪፈራል መንገዱ በተጨማሪ ከድርጅቱ ጋር ያልተዛመዱ ተዋናዮችን መረጃን እንዲያካትት ይመከራል ። ከየትኛው ድርጅት ወይም አገልግሎት ምን አይነት እርዳታ ለመቀበል እንደሚመቻቸው እንዲወስኑ ከጥቃት ለተረፉት ግለሰቦች መተዉ አለበት::
  - ለለሪጅናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንሼቲቭ (RAI):-
    - ይህ በተለምዶ ለዉጪ አግልግሎት ሰጪዎችን ሪፈራልን ያካትታል:: በአሜሪካ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች የእኛን ፍላጎቶች ለማሟላት በቂ ጥራት ይኖራቸዋል ተብሎ ቢገመትም ፤ በአገልግሎቱ የሚሰጡ ቋንቋዎች እና የከፋ የስሜት ጉዳት ላይ

ያሉ ስደተኞች ጋር የመስራት ልምድ አላቸው ወይ የሚሉትን ነገሮች ከግምት ማስገባት በጣም ጠቃሚ ነዉ::

- የአካባቢ ጥበቃ ጽ / ቤቶች የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ቋሚ ሰራተኞች ፣ ማበረታቻዎች ፣ ጊዜያዊ፣የውል ወይም የቀን ሰራተኞች እንዲሁም በጎ ፈቃደኞች የአጠባበቅ ጥስት ሪፖርት ከደረሳቸዉ ወይም የአጠባበቅ ጥስት የደረሰባቸዉን ግለሰቦችን በሌላ መልኩ አግዘው ከሆነ የተለያዩ የድጋፍ አግልግሎቶችን መድረስ እንዲችሉ እንዲያረጋግጡ ይመከራል::
- ምላሽ ሰጪ አገልግሎቶችን ለመለየት እና ለማቋቋም ምሪት ከጤና ፣ የህጻናት ጥበቃ ፣ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ(WPE) የቴክኒክ አማካሪዎች ድጋፍ ይጠይቁ።

**መማር እና መልሶ የማየት ሂደት**

ሁሉም የአጠባበቅ ጥስቶች ሪፖርት ከተደረጉ በኋላ የትምህርቶችን እና ቀሪ ክፍተቶችን ለመያዝ የመማር ሂደት መከናወን አለበት ፡ ይህም ምላሾችንን ተጨማሪ ዓወዳዊ ማድረግን ሊያካትት ወይም ከጥቃት የተረፉ ግለሰቦችን ያማከለ አካሄዳችንን መልሶ ማየት ሊሆን ይችላል። ከኢቲክስ ኮምፕላይንስ ዩኒት (ECU) ድህረ ምርመራ ምክሮችን ሊያካትት ይችላል:: የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ይህን ለማድረግ ደህንነቱ አስተማማኝ በሆነ ጊዜ ከተገልጋዩ ማህበረሰብ የአጠበበቅ ጥስትን እንዴት በተሻለ ሁኔታ መከላከል እንደሚችል ግብአት መሰብሰብ አለበት::

የተሰበሰቡት መረጃዎችን መሠረት ያደረገ እና የተለዩ ማንኛውንም ዓይነት ጉዳዮችን ለመፍታት የድርጊት መርሃግብሮች መፈጠር አለባቸው ፡ ምንም እንኳን የታሰበበት ባይሆንም ከስህተቶች መማር ፣ እንደ ድርጅት መሻሻልን ለማምጣት በጣም አስፈላጊው አካል ነው ።

- የአጠባበቅ ጥሰት ሪፖርት ከተደረገ እና ከተጣራ በኃላ መደበኛ የተገኙ ትምህርቶች እና መልሶ የመመልከት ሂደት እንዲኖር እቅድ አዉጡ ።
    - ይኸንን ሂደት ከፍተኛ አመራር እንዲመራው ይመከራል። የአጠባበቅ መሪዎችንም ማካተት አለበት።
    - የአካባቢ የቴክኒክ ሰራተኞች እና የተገልጋዩችን ግብረመልሶች በመማር እና መልሶ የማየት ሂደት ውስጥ እንዲካተቱ ይመከራል።
    - ይህ ሂደት ትረጉም ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አመራሮች የአሰራር ስልቶች እንዲመሰርቱ ይመከራል ።

# የማረጋገጫ ዝርዝር

**መከላከል እና ዝግጁነት**

- እያንዳንዱ የአከባቢ ቢሮ ቢያንስ ሁለቱ የከፍተኛ አመራር አባላት የአጠባበቅ መሪ ሆነው መመደባቸውን ማረጋገጥ አለበት::
- የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ሰራተኞች ፣ ማበረታቻዎች ፣ ጊዜያዊ ፣ የውል ፣ ወይም የቀን ሠራተኞች ፣ በጎ ፈቃደኞች ፣ አጋሮች ፣ አቅራቢዎች እና ሌሎች ተባባሪዎች አግባብነት ያላቸውን የስነምግባር ፕሮቶኮሎች እና አከባቢያዊ መደበኛ የአሠራር ሂደት(SOP) አጠቃላይ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል ።
- የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ተገልጋዮች - አዋቂዎች እና ልጆች - ተገቢውን የባህርይ ፕሮቶኮሎች እና አካባቢያዊ መደበኛ የአሠራር ሂደት (SOP) ላይ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አውዳዊ እና በትምህርታቸው ደረጃ እና አረዳዳቸው ልክ የተተረጎመ መሆን አለበት።
- ስለ መደበኛ የአሠራር ሂደት(SOP) ይዘት እና ተፈላጊ የባህርይ ፕሮቶኮሎች ከፍተኛ አመራሮች ከሰራተኞች ጋር በቋሚነት ይናገራሉ።
- የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ሠራተኞች፣ ማበረታቻ፣ ለጊዜያዊ ፣ለውል ወይም ለቀን ሰራተኞች እና ለበጎ ፈቃደኞች አጠባበቅን በተመለከተ መደበኛ የዘመነ ስልጠና ተደራሽ እንዲሆኑ እና እንዲሰጣቸውም ይገባል።

**ሪፖርት አደራረግ**

- የተገልጋዩ ማህበረሰብ ግምገማ የሚካሄደው የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የመርሃ ግብር ፣የታማኝነት ወይም የአጠባበቅ ጥሰቶችን በተመለከተ ያሏቸውን አቤቱታዎች ሪፖርት ለማድረግ የሚመርጡትን መንገድ ለመለየት ነው።
- ነባር የሪፖርት ማድረጊያ ስልቶች በመከላከል መርሃ ግብር አወጣጥ በኩል ይጠናከራሉ እንዲሁም አዳዲስ የሪፖርት ማድረጊያ ስልቶች ይነደፋሉ፤ ለተገልጋይ ማህበረሰብ ግምገማ ወቅት ከተለዩ ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን መሰረት አድርጎም ይወጣል::
- የዕይታ፣ የድምጽ እና የቪዲዮ (እንደ አግባብነቱ እና የገንዘብ አቅም በፈቀደ መጠን) ግ ንኙነቶች እንዴት በባህላዊም አግባብነት ባላቸው መንገዶች ተገልጋዩች ሪፖርት ለማድረግ በቀላሉ ማግኘት እንደሚችሉ ነው።
- የሪፖርት አደራረግ ሥርዓቱን ውጤታማነት ለመፈተሽ እና ሪፖርቶችን ለመሰብሰብ እንዲቻል ከተጠቃሚው ማህበረሰብ ጋር መደበኛ የግብረ መልስ ስብሰባዎች ይካሄዳሉ።

**ሪፖርትን በፍጥነት የከፍ የማድረግ እና የማጣራት ሂደት**

- |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||The IRC staff, incentive, occassional, contract, or day workers, volunteers, partners, vendors, or other associates know how to escalate reported or sRAIected incidents of safeguarding violations against clients, as per the *Global Reporting Guidelines*.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||
- ለተገልጋዩች ከጥቃት የተረፋን ማዕከል ያደረገ ምላሽ አሰጣጥን መረዳት እና መታዘዝ ይጠበቃል :: ይህም ልጆችን የሚመለከቱ ማናቸውንም ዓይነት ውንጀላን አስገዳጅ ሪፖርት ማቅረብን ያካትታል::
- አካባቢያዊ ቡድን አቅም በፈቀደ መጠን፣ የምርምራውን ውጤት እና መወሰድ ስላለበት እርምጃ፣ ከተጠርጣሪ ወንጀለኛ እና ከጥቃት የተረፈ ግለሰብ ጋር የተደረጉ ግንኙነቶች ጨምሮ ከአጣሪው ቡድን ለሚያቀርቡ ጥያቄዎች በሙሉ ሙሉ ለሙሉ ይተባበሩ።
- የአጠባበቅ ጥሰት ሪፖርቶች የማጣራት እና የተወሰዱ እርምጃዎች በተመለከተ እንደአግባቡ ከለጋሽ አካላት ጋር መቀናጀት እንዲሁም ግንኙነት ያድርጉ።
- የአካባቢ መስሪያ ቤቶች የመረጃ አያያዝ ስርዓት እና የመረጃ ጥበቃ ፕሮቶኮሎች በቦታው እንዲኖራቸው ይገባል።

**የምላሽ እና የድጋፍ አገልግሎቶች**

- የአካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች በአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ የተቋቋሙ አነስተኛ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ የሪፈራል መንገዶችን እና የመረጃ አያያዝ ፕሮቶኮሎችን ጨምሮ ወቅታዊ የሆነ የአገልግሎት ካርታ(Mapping) ሊኖራቸው ይገባል ።

- በአካባቢው ያሉ ቢሮዎች የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኞችን የመመደብ እንዲሁም የጥቃት ሰለባዎች ቢያንስ ዝቅተኛ አገልግሎት የሚያገኙበት ወይም ዝቅተኛ የጥራት መስፈርቶችን የሚያሟሉ የጉዳይ ክትትል አገልግሎቶች የመምራት አቅም ሊኖራቸውና በ ተጨማሪም የውስጥ አቅምን ሊያመጣ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ውጪያዊ አገልግሎት ሰጪዎችን አቅም የሚያጎለብት እቅድን ሊኖራቸው ይገባል።

**የመማር እና ቆም ብሎ የማሰብ ሂደት**

- ከአጠባበቅ ጥሰት ሪፖርት አደራረግ የቀሰምናቸው ትምህርቶች እና ቀሪ ክፍተቶች በበላይ አመራር ይገኛሉ።
- የአካባቢ ቢሮዎች በኢቲክስ እና ኮምፕሊያንስ ዩኒት(ECU)፣ በቴክኒክ ሰራተኞች፣ በተገልጋዮች ወይም በሌላ አስፈላጊ ሰዎች የተሰጡትን ምክሮች ይተግብሩ።

# አባሪ 1

**ለአጠባበቅ መሪዎች የቀረበ የማጣቀሻ ደንብ (TOR)**

<u>አላማ</u>

የአጠባበቅ ስራዎችን ወጥነት እና እድገትን ለማረጋገጥ የአጠባበቅ መሪዎችን መመደብ የአካባቢው ቢሮዎች ግዴታ ነው። ይህ ማለት ግን የሙሉ ጊዜ ስራ አይደለም። መሪዎች በአጠባበቅ እንቅስቃሴዎች ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች የግንኙነትነጥብ ሆነው ያደርጋሉ ፤የአጠባበቅ አውዶችን በመመገብ ፤እንዲሀም እንደአስፈላጊነቱ የአጠባበቅ መመሪያን፣ አብነቶችን፣ ስልጠናዎችን እና ሌሎች ግብአቶችን በማሰራጨት ሂደት እርዳታ ያደርጋሉ ።

የአጠባበቅ መሪው መመደብ የአካባቢ የበላይ አመራር በአጠባበቅ ስራዎች አፈጻጸም ላይ ያለውን የባለቤት እና ሃላፊነት አይቀንስም ወይም አያጠፋውም።

<u>ዋና ዋና ሃላፊነቶች</u>

እነዚህን ሃላፊነቶች የአጠባበቅ መሪዎች በጋራ መጋራት እንዲሁም በጊዜ ሂደት ሊለዋወጡ ይችላሉ፡

- ለአጠባበቅ ግብረ ሀይል፣ለአጠባበቅ ዳይሬክተር ወይም ለሌሎች ግለሰቦች በአካባቢው የሚደረጉ የአጠባበቅ እንቅስቃሴዎችን ወቅታዊ የማድረግ እና መረጃ ለመስጠት የግንኙነት መግቢያ መሆን
- በአካባቢያዊው መርሃ ግብር ሰራተኞች ለሚነሱ ጥያቄዎች የግንኙነት ነጥብ መሆን ወይም ፣በ ሀገር አቀፍ እና/ ወይም ዓለም አቀፍ ደረጃ የአጠባበቅ ፍኖተ ካርታዎች (policies) እና እንቅስቃሴዎች ላይ ደጋፊ መሆን
- የአጠባበቅ መመርያ፣ አብነቶችን፣ ስልጠናዎችን ወይም ሌሎች ግብአቶችን እንደ አስፈላጊነቱ ዓውድ በመስጠት እና ለአካባቢው እንዲስማማ አድርጎ ማዘጋጀት ላይ መሳተፍ እንዲሁም
- የአጠባበቅ መመርያ፣ አብነቶችን፣ ስልጠናዎችን ወይም ሌሎች ግብአቶችን እንደ አስፈላጊነቱ በማሰራጨት ስራ ላይ እርዳታ ማድረግ

<u>ጊዜ በመቶኛ</u>

የጊዜአቸው ከ 5%-10% መቶኛ እንዲያውሉ ይመከራል።

<u>ለአካባቢ ቢሮ አስፈላጊ መስፈርቶች:-</u>

ከ መሪዎቹ አንዷ ሴት መሆን አለባት፣ እንዲሁም በሁሉም ጉዳዮች የጾታ ስብጥሩን ሚዛናዊ ማድረግ ግብ ሊሆን ይገባል።
የማይቻል ካልሆነ በስተቀር የአጠባበቅ መሪዎች ከአካባቢው ቋሚ ስራተኞች የተውጣጡ እንዲሁም የአካባቢውን ህዝብ ብዝሃነት የሚወክሉ መሆን አለባቸው።

<u>ተፈላጊ ችሎታዎች:-</u>

ጥሩ የአጠባበቅ መሪዎች የሚከተሉትን ሊኖራቸው ይገባል፡-

- ጠንካራ የግንኙነት ክህሎት፣
- ለጥቃት ተራፊዎችን አዘኔታ እና ርህራሄ ማሳየት፣
- ሚስጥረኝነትን መረዳት፣
- ስለ አጠባበቅ መሰረታዊ እውቀት መኖር
- የተገልጋዮችን እና የቋሚ ሰራተኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ ቁርጠኝነት እና ጥልቅ ስሜት ማሳየት እና

- በተገልጋዮች እና ሰራተኞች አመኔታ።

# አባሪ 2

**ከጥቃት የተረፉ ህጻናትን ስለ አጠባበቅ ጥሰቶች ስናነጋግር ጠቃሚ የሆኑጥቆማዎች እና መረጃዎች**

ማንኛውም ከጥቃት የተረፉ ህጻናት ጋር መስተጋብር ለመፍጠር የሚደረግ አቀራረብ ከተለያየ ዳራ የመጡ ተገልጋዮች በድጋሚ ቀውስ ውስጥ እንዳይገቡ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ባህላዊ እና ማኅበረሰባዊ ልማዶችን ከግምት ያስገባ ሊሆን ይገባዋል።

|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||See attached PPT[8] that provides extensive and detailed information and guidance on the following:|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

- የህጻናት ጥቃትን ምንነት ለመረዳት፡- ከ1-15 ያሉ ስላይዶች እነዚህ ስላይዶች የተለያዩ አይነት የህጻናት ጥቃቶችን ፍቺ፣ ስለ ፈፃሚዎቹ ማስታወሻ እንዲሁም የተለመዱ የጥቃት ምልክቶችን ይሰጣሉ።
- ይፋ መውጣትን መረዳት፡- ከ16-21 ያሉ ስላይዶች። እነዚህ ስላይዶች ይፋ መውጣትን፣ በተንከባካቢዎች ላይ የሚደርሰውን ተጽእኖ፣ ስለሚጠበቀው ለህጻናት ተስማሚ አቀራረብ እና አገልግሎት ሰጪ እምነቶች መረጃ ይሰጣሉ።
- መሪ መርሆዎችን እና ቁልፍ ጉዳዮችን መረዳት፡-ከ22-37 ያሉ ስላይዶች። እነዚህ ስላይዶች ቁልፍ መሪ መርሆዎችን እና ቁልፍ አስገዳጅ ሪፖርት የሚደረግባቸው ጉዳዮችን ፣ የፕሮቶኮሎች ምስጢራዊነት እና የህፃናት ሁለንተናዊ ጥቅም ማረጋገጥላይ አጠቃላይ እይታ ይሰጣሉ።
- ከጥቃት የተረፉ ህጻናት ጋር የሚኖረውን ግቡቡነትን ጠቀሜታን መረዳት፡- ከ38-81 ያሉ ስላይዶች። እነዚህ ስላይዶች አበረታች ግንኙነቶች እንዴት እንደምንመሰርት፣ በጎ ልማዶች እንዴት እንደምናዳብር፣ ንግግር አልባ ስልቶች አጠቃቀምን፣ አብነት የሚሆኑ ጽሁፎችን፣ በተለያየ እድሜ ላይ ያሉ አካል ጉዳተኛ ህጻናትን ቃለመጠይቅ እንዴት እንደምናደርግ የሚጠቅሙ መርሆችን፣ ስለጥቃቱ ማውራት የማይፈልጉ ወይም ጥቃቱን የሚክዱ ከሆነ ምን ማድረግ እንደሚገባ መረጃዎችን ይሰጣሉ።
- የጉዳይ አያያዝን መረዳት:-ከ82-146 ያሉ ስላይዶች፡እነዚህ ስላይዶች የጉዳይ አያያዝ ማሰተዋወቅን እና መስተጋብርን ፣ቅበላ እና ግምገማን ፣ የጉዳይ አሰራር ዕቅድ እና አፈፃፀምን ፣ የጉዳይ ክትትል እና አዘጋግ ደረጃዎች ላይ መረጃ እና ምሪትን ይሰጣሉ።
- |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Understanding Psychosocial Interventions for Children – slides 147-152: These slides provide information on providing healing education, relaxation training, coping skills and problem solving |||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

ከስራ ባልደረባዎች፣ አዋቂዎች ወይም ከህጻናት ተገልጋዮች የሚመጡ የአጠባበቅ ጥሰት ጥቆማዎችን እንዴት ተቀብሎ ማስተናገድ እና ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ስልጠናዎችን ጨምሮ አጫጭር የመመሪያ ግብአቶች በዝግጅት ላይ ሲሆን በሁሉም የዓለም አቀፉ የነፍስ አድን ኮሚቴ ክፍሎች መካከል እ.ኤ.አ ከሰኔ/ሐምሌ 2019 ጀምሮ የሚጋሩ ይሆናል።

8 ይህ፣ ከኢንተር ኤጀንሲ የጉዳይ አስተዳደር እና ህፃናት ጥበቃ መመሪያዎች የተወሰደው ነው።

http://www.cpcnetwork.org/wp-content/uploads/2014/08/CM_guidelines_ENG_.pdf and Caring for Child Survivors of Sexual Abuse https://gbvresponders.org/response/caring-child-survivors/

# አባሪ 3

*ይህ አባሪ በተለይ የተዘጋጀው ለክራይስስ ሪስፓንስ ሪካቨሪ ኤንድ ዲቾሎፐመንት( ሲ.አር. አር.ዲ) ታዳሚዎች ሆኖ የ ሲ.አር. አር.ዲ የክወና አውዶች ክፍተቶች ከሪጂናል አንቲ ኮራፕሽን ኢንቬቲብ( አር.ኤ. አይ)ውስጥ ካሉት በእጅጉ እንደሚለዩ እውቅና ለመስጠት ነው። አር.ኤ. አይን በሚመለከት የአነስተኛ አገልግሎቶች ክፍልን ብቻ ይመልከቱ።*

**|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Minimum Care and Services Response for Survivors of Safeguarding[9] Violations|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||**
|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||In addition to adequate reporting and investigation mechanisms, the IRC is committed to providing a minimum standard of care and services to support a survivor's recovery.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||[10]
|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||This document sets out the **minimum standards for care and response services for individuals experiencing all forms of abuse and exploitation** (physical, emotional, sexual) at the hands of IRC staff, incentive, occassional, contract, or day workers, volunteers, partners, vendors, and other associates.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END||| ይህም ከጥቃት ለተረፋ ሰው እድሜ፣ የእድገት ደረጃ እና ጾታን ያማከለ ጊዜውን የጠበቀ እና ተገቢ ድጋፍ መስጠትን ያረጋግጣል፡፡

|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**<u>What</u> is the minimum care and service response that IRC needs to make sure survivors receive?**|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||
|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Upon self-disclosure by the survivor, third person report (with consent of the survivor for adults and older adolescents capable of making their own decisions), or direct observation of abuse (with consent of the survivor for adults and older adolescents), the survivor must immediately be appointed a **case worker**[11] who will make sure the survivor receives immediate care and services as needed, and engage in a **light-touch case management**[12] process.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

ለጉዳዩ የተመደበው ሰራተኛ ነው ከጥቃት ሰለባው ጋር በቀጥታ እየተገናኘ ግለሰቡ አስፈላጊውን እንክብካቤ እና አገልግሎት ማግኘቱን የሚያረጋግጠው፡፡ በጉዳይ ክትትል  የሰለጠኑ ሰራተኞች በተለምዶ ነባር  የህጻናት ጥበቃ፤ የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሐ ግብር ቡድኖች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በተቻለ መጠን  አነስተኛ የምላሽ መመዘኛዎች ነባር ቡድኖች እና የመርሐ ግብር መዋቅሮች በጉዳዩ ዙርያ እውቀት እና ተሞክሮ ስላላቸው እንዲሁም  ለሪፓርት ለማድረግ  የመጀመሪያ  መግቢያ ስለሆኑ  በእነርሱ አማካኝነት መሰጠት አለባቸው፡፡ የዓለም አቀፉ ነፍስ አድን ኮሚቴ በሚንቀሳቀስባቸው ስፍራዎች  የህጻናት ጥበቃ እና ሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሐ ግብር የሌለ ከሆነ ፣ የኮሚቴው አመራር ዝቅተኛው የምላሽ መመዘኛዎች  መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ሌሎች አማራጮችን  ለይቶ ማውጣት አለበት፡፡ ( ዝቅተኛውን የምለሽ መስፈርቶች እንዴት ማሟላት እንደሚቻል ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)

|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||The case workers' interaction with the survivor should be guided by the following **guiding principles** that also inform decision making on services, and ensures overall quality of care and that are in line with interagency humanitarian guidelines:|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

---

[9] ይህ የወሲባዊ ጥቃት እና ብዝበዛን  እንዲሁም የሕፃናት አጠባበቅን ያካትታል

[10] ኢንተር ኤጀንሲ የጉዳይ አስተዳደር እና የሕፃናት ጥበቃ መመሪያዎች http://www.cpcnetwork.org/wp-content/uploads/2014/08/CM_guidelines_ENG_.pdf, Caring for Child Survivors of Sexual Abuse https://gbvresponders.org/response/caring-child-survivors/; and Interagency Gender-Based Violence Case Management guidelines https://gbvresponders.org/response/gbv-case-management/

[11] በተለምዶ የሥነ- ልቦና ወይም ማህበራዊ ሰራተኛ የሆነው የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ ፣  ከጉዳዩ ጅማሬ እስከ ፍጻሜው ድረስ ከጥቃት የተረፈውን ሰው የመንከባከብ ሃላፊነቱን የሚወስድ ይሆናል። ይህ በተገቢው መልኩ የሠለጠነ እና ክትትል የሚደረግበት ሠራተኛ መሆን አለበት ። ለአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ፣ ይህ በተለምዶ የሕፃናት ጥበቃ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና የማብቂያ ጉዳይተከታታይ ሠራተኛ ይሆናል ።

[12] በቀጥታ ማህበራዊ-ሥራ ዓይነት ድጋፍን በመጠቀም ከጥቃት የተረፈውን ሰው የሚረዳ የተዋቀረ ሂደት ።  ከጥቃት የተረፈው ሰው መረጃ እንዲኖረው ፣የሚያጋጥሙትን ችግሮች መፍትሔ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፣ እና  ስሜታዊ ድጋፍ  በሂደቱ ሁሉ ለመስጠት፣ የስነ ልቦና ወይም የማህበራዊ ሰራተኛውን ሃላፊነት መውሰድ ያካትታል።

| ከጥቃት ለተረፉ ሴቶች እና ልጃገረዶች[13] | ከጥቃት ለተረፉ ህጻናት[14] | ከጥቃት ለተረፉ አዋቂ ወንዶች[15] |
|---|---|---|
| ከጥቃት የተረፉትን ያማከለ | ለህጻናትን ሁለንተና ጥቅም መሟገት | ከጥቃት የተረፉትን ያማከለ |
| የደህንነት መብት | የህጻኑን ደህንነት ማረጋገጥ | የደህንነት መብት |
| ምስጢር የመጠበቅ መብት | ህፃኑን ማፅናናት | ምስጢር የመጠበቅ መብት |
| የራስን ጉዳይ በራስ የመወሰን እና የክብር መብት | ተገቢ ምስጢረኝነትን ማረጋገጥ | የራስን ጉዳይ በራስ የመወሰን እና የክብር መብት |
| ያለ አድልዎ | ህጻኑን ውሳኔ አጠጣጥ ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ | ያለ አድልዎ |
| ምንም ጉዳት አለማድረስ | ሁሉንም ህጻናት በፍትሃዊነት እና በእኩልነት ማየት | ምንም ጉዳት አለማድረስ |
| | የህጻናትን የመቋቋም አቅም ማጎልበት | |

|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Once a case worker has been appointed to the survivor, the case worker should conduct a light-touch case management process consisting of the following **steps**:|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

1. |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Greet and comfort the survivor – this is the case worker's first chance to develop rapport with the survivor (and in the case of child survivors with their caregiver) and begin to develop a trusting relationship.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END||| ይህ ከጥቃት ተራፊዎች የመታመን እና የእንክብካቤ ስሜት እንዲሰማቸው እንዲሁም ከጥቃቱ ጋር በተያያዘ እራሱን / እራሷን ፤ በተጨማሪ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ያላቸውን ፍላጎት እንዲገልፁ ለማድረግ አስፈላጊ ነው ።

2. |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Obtain informed consent (and/or assent in the case of child survivors and depending on the age and development stage of the child) – it is essential for the survivor (and in the case of child survivors, their caregiver) to understand what is going to happen, understand the options for care and services and related benefits and risks, and to obtain permission to proceed.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END||| ለእያንዳንዱ ቀጣይ የአገልግሎት ሪፈራል ራሱን የቻለ ፈቃድ/ማረጋገጫ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

3. |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Conduct the following assessments:|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||
   i. የደህንነት ፍላጎቶች ፤በዚህም ከጥቃት ተራፊው ደህንነቱ መጠበቁን፣ ከወንጀለኞች ቀጣይ ጉዳት እና ከሌሎች የበቀል ጥቃት እና መገለል መራቁን ማረጋገጥ
   ii. የጤና ፍላጎቶች፣ በዚህም አስቸኳይ ወይም አስቸኳይ ያልሆነ የህክምና እርዳታ ወይም ሪፈራል አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ
   iii. የስነ ልቦናዊ እና ማኅበራዊ ፍላጎቶች፣ በዚህም አሁን ላይ የጥቃት ተራፊው አጠቃላይ አኳኋን ደረጃ ራስን የመጉዳትና የማጥፋት ራስን የማጥፋት ጨምሮ የህክምና እና/ወይም ደህንነት ስጋቶች የሚያመጣ አለመሆኑን መገምገምን

[13] ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መከላከል (GBV) የኃላፊነት ወሰን (AOR) ዝቅተኛ መመዘኛዎች (መጨው) እና የድርጅቶች ጥምረት/የኢንተር ኤጀንሲ/ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ጉዳይ አስተዳደር መመሪያዎች ለማግኘት ፡-https://gbvresponders.org/response/gbv-case-management/

[14] የድርጅቶች ጥምረት/ኢንተር ኤጀንሲ/ የጉዳይ አያያዝ እና የሕፃናት ጥበቃ መመሪያዎች http://www.cpcnetwork.org/wp-content/uploads/2014/08/CM_guidelines_ENG_.pdf and Caring for Child Survivors of Sexual Abuse https://gbvresponders.org/response/caring-child-survivors/

[15]ከወሲባዊ ጥቃት የተረፈ ወንድን በተመለከተ የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ መመሪያ፤ ከአስገድዶ መድፈር ለተረፉ የዓለም ጤና ድርጅት የህክምና አያያዝ ፡- https://www.who.int/reproductivehealth/publications/emergencies/924159263X/en/

እና የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ከወሲባዊ ጥቃት የተረፈ የህክምና እርዳታ ፡- https://gbvresponders.org/response/clinical-care-sexual-assault-survivors/

iv. የህግ/የፍትሕ ፍላጎቶች፣ የጥቃት ተራፊው (እና ከጥቃት ተራፊው ህጻን ከሆነ ደሞ ተንከባካቢው) ባለው የፍትሕ ስርዓቶች በመጠቀም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ፍላጎት አለው ወይ? የሚለውን መወሰን

4. **|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Develop a case action plan based on the main and immediate needs and based on the wishes of the survivor (and in the case of child survivors, their caregiver) in terms of what services will be required.**|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||**

5. **|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Provide or refer to the required services in the four main areas of assessment with priority needs and minimum services as required in bold:**|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||**
   i. |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Safety and protection** from further abuse |||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||
   **ii. ብቁ የጤና እንክብካቤ እና ህክምና**
   iii. |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Immediate** and longer term **psychosocial support**|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||
   iv. የፍትህ ተደራሽነት

6. |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Follow up and monitoring to ensure the survivor has received needed services and to assess any improvement in the survivor's situation.**|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||** ቀጣይ የክትትል ስብሰባዎች የጥቃት ትራፊው እና ጉዳዩን የሚከታተለው ሰራተኛ ከመጀመርያው ስብሰባ በኋላ ስለተወሰዱ እርምጃዎች መረጃዎችን እንዲለዋወጡ እንዲሁም ከሌሎች ጉዳዩች መሀል ቀጣይ የረጅም ጊዜ ፍላጎቶችን እና እንክብካቤዎች ላይ ለመወያየት ያስችላሉ ፡ በተጨማሪም የክትትል ስብሰባዎች የጥቃት የጉዳይ ተከታታዩች የጥቃት ተራፊውን የደህንነት ሁኔታ መልሰው እንዲገመግሙ እድል ይሰጣሉ።

|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Minimum services across the four main areas** included:|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

ደህንነት

- |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Safety action plan**: If during the assessment it is determined that the survivor is not safe, the case worker should prioritize with the survivor the development of a safety action plan including a combination of referrals to protection and security agencies, and the development of an individual safety plan|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

ጤና

ወሲባዊ እና አካላዊ ጥቃት ለደረሰባቸው የጥቃት ተራፊዎች ግምገማ ወቅት የህክምና አገልግሎት እንደሚያስፈልግ ወይም አያስፈልግ እንደሆነ መወሰን ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። የህክምና አገልግሎት አጣዳፊነት ጉዳት ሲኖር እና/ወይም የህመም አቤቱታ እና/ወይም ጥቃቱ የተፈፀመበት ጊዜ እና/ወይም የጥቃቱ አይነት እና / ወይም ማስረጃ አሰባሰብ ይወሰናል ። ወሲባዊ ጥቃት ባለፉት 120 ሰአታት ውስጥ ከተከሰተ፣ ይህ ህይወትን አድን እርምጃዎች ለመስጠት ወሳኝ ጊዜ ውስጥ ስለሆነ አስቸኳይ የህክምና እርዳታ አገልግሎቶች ያስፈልጋሉ። 120 ሰአታት በላይ ካለፉ በኃላ ጉዳት እና ህመም ካለ የሕክምና አገልግሎቶች አሁንም አስቸኳይ ሊሆኑ ይችላሉ። **|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Urgent (e.g. immediate) medical services** may be necessary for:**|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||**

- ኤች.አይ.ቪን መከላከል፡- የጥቃት ተራፊው ለኤችአይቪ ኢንፌክሽን ከተጋለጠ ወደ ህክምና ማእከል ተልኮ ለቫይረሱ መከላከያ የሚወሰደውን መድኃኒት በ 3 ቀናት ውስጥ (በ 72 ሰዓታት) ከወሰደ በቫይረሱ የመያዙ እድል ይቀንሳል።
- እርግዝናን መከላከል፡- የጥቃት ተራፊዋ ከጥቃቱ በኋላ ወደ ህክምና ማእከል ተልካ በአምስት ቀን (በ 120 ሰዓታት ውስጥ) ውስጥ የድንገተኛ ጊዜ የወሊድ መቆጣጠርያ ከወሰደች ላልተፈለገ እርግዝና የመጋለጥ እድሏ ይቀንሳል።

- ለጽኑ ጉዳት ወይም ህመም የሚደረግ የህክምና ማረጋጋት/እርዳታ፡ እንደ ጉዳቱ መጠን እና ዓይነት (ማለትም የአጥንት ስብራት፣ ቁስል ወይም ውስጣዊ ጉዳቶች) አስቸኳይ የህክምና ትኩረት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡
- መስረጃ ማሰባሰብ፡- የጥቃት የተረፈው ለሕጋዊ ዓላማዎች ማስረጃ እንዲሰበሰብ ከጠየቀ በተቻለ ፍጥነት (በ48 ሰዓታት ውስጥ) የህክምና ምርመራ መዘጋጀት እና መዘገብ አለበት፡፡ ከጥቃት ተራፊዋ ካልታጠበ/ቸ ወይም መጸዳጃ ቤት ካልሄደ/ቸ የወንድ ዘር ፈሳሽ (ስፐርም) ከአፍ ውስጥ እስከ 12 ሰአታት፣ ከሴት ብልት ውስጥ እስከ 48 ሰአታት ሊሰበሰብ ይችላል ፡ የወንዱ ብልት ወደ ውስጥ ካልገባ የወንድ ዘር ፈሳሽስ በሰውነት ላይ እስከ 6 ሰአታት መገኘት ይችላል፡፡ ጉዳቶች በዝርዝር መመዝገብ አለባቸው፡፡
- አንዳንድ ለህይወት አስጊ የሆኑ ጉዳቶች ምንም አይነት አካላዊ ምልክት ስለማያሳዩ እና ህመም ስለማይኖራቸው (ማለትም የውስጥ ሰውነቶች ክፍል ደም መፍሰስ እንደ ሆድ ዕቃ ወይም አንጎል ፣ፊስቱላ፣ ወዘተ ያሉ) በቀላሉ ሊለዩ እንደማይችሉ እባክዎን ልብ ይበሉ ፡፡

ግለሰቡ/ቧ ከጉዳት ወይም ህመም ነጻ ከሆነ/ች፣ ወሲባዊ ጥቃቱ ከ 120 ሰአታት በፊት ከተፈጸመ እና/ወይም የጥቃቱ አይነት አካላዊ ጉዳት፣ ንክኪ ወይም የብልት ውስጥ መግባት ካላካተተ የሕክምና አገልግሎቶች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ ግን አስቸኳይ አይደሉም ፡ ወሲባዊ ጥቃት ከተፈጸመ ከ 120 ሰዓታት በኃላ እንክብካቤ የሚሹ የጥቃት ተራፊዎች የህክምና እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ስለሚችል ህክምና እንዳያገኙ ማዘግየት ወይም ተስፋ ማስቆረጥ አይገባም ፡፡ አስቸኳይ ያልሆነ የህክምና አገልግሎት ለሚከተሉት ነጥቦች አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡-

- ክላሚድያ፣ ጨብጥ እና ቂጥኝን ጨምሮ በግብረስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ አባላዘር በሽታዎች በጊዜ ካልታከሙ ሥር የሰደደ በሽታ ወይም መካንነትን ስለሚያስከትሉ በአንቲባዮቲኮች መታከም አለባቸው ፡፡
- ሽንት ወይም ሰገራን መቆጣጠር አለመቻል የቀዶ ጥገና ትኩረት የሚፈልጉ እንደ ፌስቱላ እና ፊንጢጣ ያሉ ከባድ ውስብስብ ጉዳቶችን የሚያመላክቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||Comprehensive abortion care, depending on the needs and wishes of the survivor[16].|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

ማኅበራዊ ስነ ልቦና

- |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Self-harm and Suicide assessment and/or crisis intervention**: Survivors may experience very serious reactions to the experience of abuse, particularly sexual abuse.|||UNTRANSLATED_CONTENT_END||| ለጉዳዩ ታከታታይ ሰራተኛ ከጥቃት ተራፊው ራስን የመጉዳት ወይም ራስን የማጥፋት አደጋ ተጋላጭ መሆኑን የሚጠቁሙ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን በትኩረት መከታተል አስፈላጊ ይሆናል ፡፡ የክትትል እርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ ፡- ራስን የመጉዳት/ራስን የማጥፋት እሳቤዎች በቅርብ ወይም በሩቅ ጊዜ መከሰታቸዉን መዳሰስ፣ አደጋዎችን መመርመር፣ ስሜትን መረዳት እና ድጋፍ መስጠት፣ እንዲሁም የጥንቃቄ መርሀ ግብር መንደፍ፡፡ ከጥቃቱ ተራፊው አፋጣኝ እርዳታ በሚያስፈልገዉ የቀዉስ ሁኔታ ዉስጥ መሆኑን ከተረዳህ በፍጥነት ወደ ጤና ጣቢያ እንዲሄድ ወይም ከአደጋ ወደጸዳ እና ክትትል ሊደረግበት ወደሚችል ቦታ እንዲሄድ ማመቻቸት፡፡
- |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Emotional support**: this may happen through the non-judgmental, survivor-centered engagement of the caseworker with the survivor and include the basics of Psychosocial First Aid|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||
- |||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**Providing basic education about abuse**: this helps survivors understands and manage their reactions, and provides them with very specific information about the impact of abuse and the strategies to manage the impact of the abuse|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||
- የጥቃቱ ትራፊዎችን በተለየ ችግሮቻቸዉ ላይ መርዳት፡- ግለሰቦች ጥቃት እንደደረሰባቸው ማህበረሰቡ በሙሉ ካወቀ የሚያስከትለው ጎጂ መዘዝ አይቀሬ ነው ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ከጥቃት የተረፉ ህጻናት በደረሰባቸዉ ወሲባዊ ጥቃት ምክንያት በተለይ እርግዝና ከተከሰተባቸዉ ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመለሱ ክልከላ ሊደረግባቸዉ ይችላል፡፡ ያላገቡ ሴቶች እና ኮረዳ ልጃገረዶች በሚደርስባቸዉ ጫና ምክንያት ከወንጀለኛዉ ጋር በትዳር እንዲጣመሩ ሊገደዱ ይችላሉ ወይም ሌሎች በቤተሰብ ደረጃ

[16] https://rescuenet.rescue.org/Interact/Pages/Section/SubFullOne.aspx?subsection=8528&SearchId=377821

የሚፈጸሙ ስምምነቶች ሊጫኑባቸዉ ይችላል፡፡ ያገቡ ሴቶች በቤተሰባቸዉና በአካባቢዉ ማህበረሰብ መገለል ሊደርስባቸዉ ይችላል፤ እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች ክብርን ለማስጠበቅ በሚል ግድያ እና ሌሎች ጉዳቶች ሊፈጸሙባቸዉ ይችላል፡፡ ከጥቃት  የተረፉ ሰዎች ወደ አምልኮ ቦታ ለመሄድ ወይም በሚኖሩበት አካባቢ ባጠቃላይ ለመታየት ሀፍረት ሊሰማቸዉ ይችላል ወይም ሌሎች ግላዊ የሆኑ ችግሮች ሊገጥማቸዉ ይችላል፡፡ ከጥቃት የተረፉ ሰዎች ከደረሰባቸዉ ጥቃት ለማገገም አንዱና በጣም ወሳኙ መንገድ የእለት ከእለት መደበኛ እንቅስቃሴያቸዉን መቀጠል ነዉ ለምሳሌ፡- እንደ ትምህርት ቤትና ሌሎች ደህንነታቸዉ የተጠበቁ ቦታወች ላይ ጊዜያቸዉን ማሳለፍ፣ ከሌላ ሰዉ ጋር ወደ ገበያ ቦታ መሄድ እንዲሁም ሀይማኖታዊና ማህበረሰባዊ በሆኑ ስብሰባወች ላይ ተሳትፎ ማድረግ ነው፡፡ የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኞች  ከጥቃት የተረፉ ሰዎች ከጓደኞቻቸዉ፣ ከቤተሰቦቻቸዉ እና ከአካባቢዉ ማህበረሰብ ጋር የነበራቸዉን ግንኙነት መልሶ ለመገንባት/ለመጠገን ሊረዱ የሚችሉ ስልቶችን ለመንደፍ  በጋራ መ ስራት አለባቸዉ፡፡

- ከጥቃት  የተረፉ ህጻናትን በተመለከተ ለእንክብካቤ ሰጪው እና/ወይም ለሌሎች የቤተሰብ አባላት የምክር አገልግሎት መሰጠት ያስፈልጋል፡፡ ከጥቃት  የተረፉ ህጻናት በዙሪያቸዉ የሚገኙ የቅርብ ሰዎች የአቀራረብ መንገድ  ስሜታቸዉን ሊነካ ይችላል፡፡ አብዛኞቹ ወላጆች ልጆቻቸዉ ጥቃት እንደደረሰባቸዉ ሲያዉቁ በተለይ ወሲባዊ ጥቃት ከሆነ ጠንካራ ስሜት ያሳያሉ፡፡ ጥቃትን በተመለከተ ወላጆች ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ሊኖራቸዉ ስለሚችል ጥቃት የደረሰባቸዉን ልጆቻቸዉን ሊወቅሱ ይችላሉ ወይም ሊናደዱባቸዉ ይችላሉ፡፡ ይህ ከተከሰተ የጉዳይ ተከታታይ  ሰራተኞች  ለተጎጅ ቤተሰብ የምክር አገልግሎ መስጠት ሊኖርባቸዉ ይችላል፡፡ የምክር አገልግሎቱ ጥቃት የደረሰባቸዉ ልጆች ተንከባካቢዎች በግልጽ (ልጆቹ ባሉበት ሳይሆን) በልጆቹ ላይ የደረሰባቸዉ ጥቃት ያሳደረባቸውን ስሜት እና ይህም ምን ዓይነት ተጽዕኖ  እያደረሰባቸዉ  እንደሆነ   እንዲያጋሩ፤  እንዲሁም  ተንከባካቢዎች  ለራሳቸዉ  እና  ጥቃት ለደረሰባቸዉ ልጆቻቸው በምን መልኩ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸዉ እሚያስችል መረጃ፣ ድጋፍ እና ትምህርት መስጠት በሚያስችል መልኩ ትኩረት ማድረግ አለበት፡፡

<u>ህጋዊ</u>

ፍትህን ለመግኘት መወሰን ታላቅ ነዉ፤ ከጥቃት  የተረፉ ሰዎች (ህጻናት ከሆኑ ተንከባካቢወቻቸዉ) ይኸን ውሳኔ በደንብ እንዲያሰላስሉት  የተሟላ የመረጃ ተደራሽነት ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ ከጥቃት  የተረፉ ሰዎች ወይም ቤተሰቦቻቸዉ እዚህ ዉሳኔ ላይ ለመድረስ የተወሰነ ጊዜ ሊወስድባቸዉ እንደሚችል የታወቀ ነዉ፡፡ በመጀመሪያዉ የጉዳይ ድርጊት መርሀ ግብር ወቅት ፣ የህግ አማራጮችን ከጥቃት  ለተረፉ ሰዎች  ማቅረብና በአማራጮች ዙሪያ እንዲመክሩበት ጊዜ መስጠት ፍጹም ተቀባይነት ያለዉ አካሄድ ነዉ፡፡

|||UNTRANSLATED_CONTENT_START|||**<u>How</u> do we make sure survivors receive the minimum care and service response?**|||UNTRANSLATED_CONTENT_END|||

| **የአነስተኛ እንክብካቤ እና አገልግሎቶች ትግበራ** | **የአነስተኛ አፈጻጸም ደረጃ መለኪያ አመላካች** | **አነስተኛ ደረጃን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች** | **ማረጋገጫ** |
|---|---|---|---|
| የአነስተኛ እንክብካቤ እና አገልግሎቶች ትግበራ ቁጥር 1: - አገልግሎቶችን ጠቋሚ ካርታ ሥራ | ከጥቃት የተረፉ ግለሰቦችን ፍላጎቶች በበቂ ሁኔታ ያሟላሉ ተብለው በተገመገሙ ጤናን፣ጾታን መስረት ያደረገ ጥቃት(GBV) እና የህፃናት ጥበቃ | • መደበኛ የአሰራር አካሄዶችን እና የአካባቢያዊ አገልግሎቶችን መገኛ የሚያብራሩ የረፈራል ጠቋሚዎችን ለማግኘት የጤና፣ጾታን መስረት ያደረገ ጥቃት እና የህጻናት ጥበቃ ዘርፎችን ይጠይቁ፡፡<br>• መደበኛዉን ፈጣን የአገልግሎት ምልከታ ካርታ ንድፍ አብነትን በመጠቀም የጤና፣ጾታን መስረት ያደረገ ጥቃት እና የህጻናት ጥበቃ አገልግሎት ሰጭዎችን ቃለ- | \|\|\|UNTRANSLATED_CONTENT_START\|\|\|Mapping available here\|\|\|UNTRANSLATED_CONTENT_END\|\|\| |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | አገልግሎትን ጨምሮ በሁለት ሰአት የጉዞ ክልል ዉስጥ በሚገኙ የፕሮጀክት ጣቢያው የሚያካትት በየስድስት ወራቱ የሚጠናቀቅ ፈጣን የአገልግሎት አመላካች ንድፍ | መጠይቅ በማድረግ ፈጣን የአገልግሎት ምልከታ አካሂድ። <br>• አንድ ከጥቃት የተረፈ ግለሰብ ከፕሮጀክቱ የትግበራ ጣቢያ እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ሊወስድበት እንደሚችልም ገምግም። (ከሁለት ሰአት በላይ ከወሰደ ከጥቃት የተረፈው ግለሰብ ወቅታዊ እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ አገልግሎት የማግኘት እድሉ አነስተኛ ስለሚሆን አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ በቀጥታ አገልግሎት አቅርቦት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ይኖርበታል - እርምጃ ቁጥር 3ን ይመልከቱ) <br>• xxxን በመጠቀም የአገልግሎቶችን ጥራት ፈትሽ:: አገልግሎቶች እነዚህን መስፈርቶች የማያሟሉ ከሆነ አለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ በቀጥታ አገልግሎት አቅርቦቶች ላይ የመዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ ይኖርበታል። ትግበራ ቁጥር 3ን ይመልከቱ። ጥራትን ለመፈተሽ ግብረ ሀይል በቡድኑ ዉስጥ እንደሚያስፈልግ ልብ ይበሉ። | |
| አነስተኛ እንክብካቤና አገልግሎት ትግበራ ቁጥር 2፡ የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ መመደብ | ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ ከተመሳሳይ ወይም በጣም ቅርብ ከሆነ ስፍራ በ 24 ሰዓታት ውስጥ ይመደባል። | • የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የህጻናት እንክብካቤ ፕሮግራም እና/ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ( WPE) ፕሮግራሞች ትግበራ ላይ ከሆኑ፣ የህጻናት እንክብካቤ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ ነበር የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኞች ከጥቃት የተረፉ ግለሰቦች በአካባቢዉ ወይም በጣም ቅርብ ከሆነ አካባቢ ሊደርሱባቸዉ የሚችሉ ድንገተኛ ሁኔታዎ ች ለመከላከል እንዲቻል | ለእያንዳንዱ ጉዳይ የተወከለዉን የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ ስም እና የምደባ ቀን የሚያረጋግጥ መዝገብ … ላይ ይገኛል (ከጥቃት የተረፈዉን ግለስብ ማንነት የሚገልጽ መረጃ ሳይኖረዉ)። <br><br>የህፃናት ተንክብካቢ ላልሆኑ/የ በሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ ጉዳይ ተከታታይ ሰራተኞች እና/ወይም ዉጫዊ አገልግሎት አቅራቢዎችን የሚመለከት የስልጠና ሰነድ (ለምሳሌ ቀን፣ አጀንዳ እና የስልጠናዉ ተሳታፊወች ዝርዝር)… ላይ ይገኛል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | መመደብ ይገባቸዋል። እንደ አጠቃላይ መመሪያ፣ ለህጻናት ለሚደረጉ የአጠባበቅ ጉዳዩች የህጻናት እንክብካቤ ጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ፣ የአጠባበቅ ጥሰቶችን ለመከላከል ደግሞ የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ (WPE) ጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ መወከል። የዚህ ቡድኖች/የስራ ባልደረቦች በወንጀል ድርጊቶች ተሳትፎ አላቸዉ ከተባለ የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ ከተቃራኒ ቡድን መወከል (ይህ ማለት የህጻናት እንክብካቤ ሰራተኛ የወንጀል ተሳትፎ ካለዉ የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ ጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛን ለህጻናት አጠባበቅ መመደብ፣ ሁኔታዉ በተቃራኒዉ ከሆነም በተመሳሳይ መልኩ ከተቃራኒ ቡድን ሰራተኛ መመደብ)<br>• የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የህጻናት እንክብካቤ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሃግብሮች ከሌሉ የአገሬው ቡድን ከተመሳሳይ ቦታ ወይም በጣም ቅርብ ከሆነ አካባቢ የሚገኙ ሌሎች የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ሰራተኞች እንደ ጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛ ሆነዉ ማገልገል ይገባቸዋል ወይስ አይገባቸዉም የሚለዉን መለየት ይገባዋል (ለምሳሌ የጤና ወይም የትምህርት ሰራተኞች)።<br>ይህን ቀደም ብሎ መለየት፣ እነዚህ ሰራተኞች (ስለ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ስለ ጉዳይ አያያዝ እና ብቁ እንክብካቤ ) አግባብነት ያለዉ ስልጠና ቀደም ብለዉ እንዲያገኙ ይረዳል። በዚህ ጉዳይ የቴክኒካል ድጋፍ እና ክትትል በህጻናት እንክብካቤ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ወይም በሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ የቴክኒክ ረዳቶች መሰጠት አለበት። <br>• የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የህጻናት እንክብካቤ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሃግብሮች በቦታው ከሌሉ እና እንደ ጉዳይ ሰራተኛ ሆነዉ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሌሎች የአለም አቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ ሰራተኞች ከሌሉአመላካቹ ካርታ የትኛውን የውጭ አገልግሎት አቅራቢ እንደ ጉዳይ ሰራተኛ ሆነዉ ሊመደቡ እንደሚችሉ ማመላከት አለበት። ይህ አስቀድሞ ተለይቶ መታወቅ አለበት ፤በመሆኑም እነዚህ አገልግሎት ሰጭዎች በመሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ስለ ጉዳይ አያያዝ እና ብቁ አገልግሎት አግባብነት ያለዉ ስልጠና ቀደም ብለዉ እንዲያገኙ ይረዳል። በዚህ ጉዳይ የቴክኒካል ድጋፍ እና ክትትል በህጻናት እንክብካቤ ወይም በሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ የቴክኒክ ረዳቶች መሰጠት አለበት። | |
| አነስተኛ እንክብካቤና አገልግሎት ትግበራ ቁጥር 3፡ አነስተኛ የጥንቃቄ እና እንክብካቤ፣ አስቸኳይ ብቁ የጤና እንክብካቤ እና ህክምናን ፣ እና ፈጣን ማህበራዊ - የስነልቦናዊ አገልግሎቶች በቀጥታ ማቅረብ እና/ወይም እነዚህን | የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኞች በተመደቡ በ24-36 ሰአታት ዉስጥ የደህነት፣ የጤና፣ የማህበራዊ - ስነልቦና እንዲሁም የህግ ፍላጎቶች ዳሰሳ መጠናቀቅ አለበት። | • የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ የጤና፣ የህጻናት ጥበቃ እና/ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ (WPE) መርሃ ግብሮች መሰረታዊ አገልግሎቶችን በሚሰጡበት በተመሳሳይ ቦታ ወይም ተቀባይነት ባለው ርቀት ስፍራ፣ ከጥቃት የተረፈው ግለሰብ እነዚህን አገልግሎቶች ማግኘቱን የጉዳይ ተከታታይ ሰራተኛው ያረጋግጣል። <br>• የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ የተወሰነውን ወይም ሁሉንም እነዚህ አነስተኛ አገልግሎቶችን የማይሰጥ ከሆነ ፣ ወይም ከጥቃት ለተረፈው ግለሰብ | የግምገማውን ቀን፣የአገልግሎት አሰጣጡን/የሪፈራሉን ቀን እና አይነት፣ እና ለእያንዳንዱ ግለሰብ ጉዳይ የክትትል ስብሰባውን ቀን የሚያመለክት ሰነድ የሚገኘው...(ከጥቃት ሰለተረፈው ጠቋሚ መረጃ የሌለበት) <br><br>ምንም (ወይም በቂ ያልሆነ) የጤና፣ የሕፃናት ጥበቃ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሃግብሮች በሌሉባቸው አገራት፤ የሕፃናት ጥበቃን ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ ምላሽን እና / ወይም ሌሎች የምላሽ አቅምን ለመገንባት (ለምሳሌ የሰለጠነ ማህበራዊ ሰራተኛ / አማካሪ ፤ለማምጣት፣ ከጥቃት የተረፈውን እና አብሮ ተጓዥ ሠራተኛዎችን ወደ ትልልቅ ከተማ ለማጓጓዣ ገንዘብ)፤ እና / ወይም ለውጫዊ አቅም ማጠናከሪያ ስልጠና እና አቅርቦቶች የሚደረግ የገንዘብ ፍሰት እቅድ እና በጀትን የሚዘረዝር የአገሪቱ ሰነድ የሚገኘው.. <br><br>የሪፈራል እና የመረጃ አያያዝ ፕሮቶኮሎች በ… ይገኛሉ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አገልግሎቶች ወደሚያገኙበት መምራት | አገልግሎት አሰጣጥ እና/ ወይም ሪፈራል የሚከናወነው ግምገማው ባለቀ በ24 ሰአታት ውስጥ ነው።<br><br>አገልግሎት ከተሰጠ እና/ወይም ሪፈራል በተደረገ ጊዜ፣ ቢያንስ አንድ የክትትል ሰብሰባ ይደረጋል። | ተቀባይነት ባለው ርቀት ላይ ካልሆኑ ፣ ወይም ግለሰቡ የውጭ አገልግሎቶችን ማግኘት በሚፈልግበት ጊዜ ፣ ከጥቃት የተረፈው ግለሰብን እንዲልክ ፣ የአገልግሎት አመላካቹ የትኛው የውጫዊ አነስተኛ አገልግሎት በቅርበት እና በጥራት የት እንደሚገኝ ለጉዳዩ ተከታታይ ሠራተኛ ማመለከት አለበት።<br>• የአለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ ፤ በአሁኑ ጊዜ እነዚህን አነስተኛ አገልግሎቶች ለማቅረብ የጤና፣ የህጻናት ጥበቃ እና/ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሃ ግብሮች ከሌሉ ፣እና የውጭ አነስተኛ አገልግሎቶች የሌሉ፣ሩቅ ወይም ዝቅተኛ ጥራት ያላቸው በሚሆኑበት ጊዜ፣ የሃገሪቱ መርሃ ግብር የሙሉ ጊዜ የህጻናት ጥበቃ ወይም የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ ጉዳይ ተከታታይ ስራተኛ ማምጣት እና በጀት ማድረግ እና/ወይም ለውጫዊ ምላሽ ሰጭዎች በጀት አዘጋጅቶ የአቅም ግንባታ ተግባራት(ለምሳሌ፤ስልጠና፣ አቅርቦቶች) ማኪያሄድ ይጠበቅበታል።<br>• በአገልግሎት አቅራቢዎች ዘንድ ያሉ የአላላክ/ሪፈራል ፕሮቶኮሎች እና የመረጃ አያያዝ መርሆዎች መደበኛ የአሰራር ሂደቶችን ለማግኘት የህጻናት ጥበቃ እና የሴቶች ጥበቃ እና ማብቂያ መርሃ ግብሮችን ያነጋግሩ። እነዚህ ከሌሉ ወይም በአነስተኛ መመዘኛዎች መሠረት ካልሆኑ፣ የአገሪቱ መርሃግብሮች እነዚህ በቦታው መኖራቸውን እና መስፈርቶቹን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |